# የምስራች

## የመጀመሪያ ደረጃ
## የደህንነት ትምህርት በክትትል
## የማስተማሪያ መጽሐፍ

### የአገልጋዩ መምሪያ



እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ።
ማቴ 11:28

ሴሊሆም ምዕራፍ ፱ አገልግሎት
ሁለተኛ ዕትም ሚያዝያ 1994 ዓ.ም.

# የምሥራች

## የመጀመሪያ ደረጃ የደህንነት ትምህርት
## በክትትል የማስተማሪያ መጽሐፍ

### የአገልጋዩ መምሪያ

ዋና አዘጋጅ መርዓዊ ሥላሴ ንጉሤ
/የተሃድሶ ክርስቲያኖች ህብረት አገልጋይ/

አድራሻ ☎ 61 29 78
09 21 58 82
✉ 110152
አዲስ አበባ

ሴሊሆም ምዕራፍ ፱ አገልግሎት
ሁለተኛ ዕትም ሚያዝያ 1994 ዓ.ም.

## ማሳሰቢያ

* በመጀመሪያ ይህች መጽሐፍ ስትዘጋጅ መንደርደሪያ የሚሆነንን አሳብ የወሰድኩት የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት ካዘጋጃት የሥልጠና መጽሐፍ ውስጥ ነበር።ነገር ግን ይህቺኛዋ በቅርጽም ሆነ በይዘት ፈጽሞ የተለየች ናት።

* እኔ በዋና አዘጋጅነት መጽሐፏን ለማዘጋጀት ብችልም ስማቸውን ለመዘርዘር የማይቻል እያሌ ሰዎች የተሳተፉ መሆናቸውን ለመግለጽ እወዳለሁ።

* በመጽሐፏ የተጠቀምኩባቸው ገላጭ ስዕሎች ሁሉም የተወሰዱት ከ Good News Bible ውስጥ ነው።

* መጽሃፏን ከስልጠና ጋር ወይም መጽሐፏን ብቻ ለማግኘት የሚፈልጉ ሁሉ በአድራሻችን ሊያገኙን ይችላሉ።


አድራሻ : መርዓዊሥላሴ ንጉሤ

☎ 61 29 78
09 21 58 82

✉ 110152
አዲስ አበባ


ሰሊሆም ምዕራፍ ፪ የወንጌል አገልግሎት


መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው


# ማውጫ

ርዕስ


የአዘጋጁ አጭር ማስታወሻ
መግቢያ ........................................ 1

## ምዕራፍ አንድ

ለአገልጋዩ
I የክትትል አስፈላጊነት ........................................ 2
II ስለ ክትትል የጌታ ኢየሱስ ምሳሌነት
ትዕዛዝና የተሰፋ ቃል ........................................ 3
III ለክትትል ከሁሉም የተሻለው መንገድ ........................................ 3
IV የቤተክርስቲያን ምሳሌነት ........................................ 4
የክትትል ትምህርት ማስተማሪያ መጽሐፉን
V እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ........................................ 5
VI ተጠንቀቅ ........................................ 6
VII ተጨማሪ መግለጫ ........................................ 6

## ምዕራፍ ሁለት

የመጀመሪያ ደረጃ የደህንነት ትምህርት
ለአገልጋዩ ........................................ 8
ትምህርት 1 : የምሥራች ........................................ 9
ትምህርት 2 : የወንጌሉ ቃል ........................................ 9
ትምህርት 3 : በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ........................................ 13
ትምህርት 4 : በክርስቶስ የማመን ዋስትና ........................................ 15
ትምህርት 5 : በክርስቶስ ትምህርት ማደግ ........................................ 17
ትምህርት 6 : ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ ........................................ 22
I: የእግዚአብሔርና የሰው ሕብረት ........................................ 23
II: የእግዚአብሔር ምህረት ........................................ 24
III: ቅድስና ........................................ 25
ትምህርት 7: መንፈስ ቅዱስ ........................................ 26

## ምዕራፍ ሦስት

በክርስቶስ የማመን ዋስትና
ለአገልጋዩ ........................................ 30
ትምህርት 8 : እግዚአብሔር ይወድሃል ........................................ 32
ትምህርት 9 : እግዚአብሔር ተቀብሎሃል ........................................ 34
ትምህርት 10 : እግዚአብሔር በአንተ አንተም በእግዚአብሔር
ውስጥ አለህ ........................................ 37
ትምህርት 11 : በእግዚአብሔር ተመርጠሃል ........................................ 38
ትምህርት 12 : ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ተጠርተሃል ........................................ 40

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ትምህርት 13 : ኃጢያትህ ተሰርዮልሃል / ተደምስሶልሃል/......42
ትምህርት 14 : የዘለዓለም ሕይወት አግኝተሃል ......44
ትምህርት 15 : የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል ......46
ትምህርት 16 : አዲስ ፍጥረት ሆነሃል ......48
ትምህርት 17 : በእግዚአብሔር ፊት ብቃትን አግኝተሃል......50

**ምዕራፍ አራት**

ደህንነት
ለአገልጋዩ......53
ትምህርት 18 : ደህንነት የእግዚአብሔር ጥበብ ......58
ትምህርት 19 : ዳግመኛ መወለድ ......61
ትምህርት 20 : ቅድስና ......64
ትምህርት 21 : ክብር ......66

**ምዕራፍ አምስት**

የእግዚአብሔር ባህርይ
ለአገልጋዩ ......69
ትምህርት 22 : እግዚአብሔር ስብዕና ያለው አምላክ ነው......70
ትምህርት 23 : እግዚአብሔር ከሁሉ የሚለይ አምላክ ነው......71
ትምህርት 24 : እግዚአብሔር ሊፈራ የሚገባው አምላክ ነው...72
ትምህርት 25 : እግዚአብሔር ሰውን ይወዳል፣ይጠብቃል......73

**ምዕራፍ ስድስት**

ቤተክርስቲያንና ስርዓቶቿ
ለአገልጋዩ......74
ትምህርት 26 : ቤተክርስቲያን / የአማኞች ህብረት / ......75
ትምህርት 27 : አምልኮ ......78
ትምህርት 28 : ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከር......80
ትምህርት 29 : ጥምቀት ......82
ትምህርት 30 : የጌታ እራት ......84

## የአዘጋጁ ማስታወሻ

ይህን የመጀመሪያ ደረጃ የደህንነት ትምህርት በክትትል የማስተማሪያ መጽሐፍ ለማዘጋጀት ያነሣሣኝን ዋናው ምክንያት ለአገልጋዮች ብቻ በሚሠጠው ሥልጠና ላይ በትምህርት መልክ ገልጨዋለሁ:: የሁልጊዜ ሐሳቤ በህይወት በምኖርበት ዘመን ለአካሉ ማለትም ለቤተክርስቲያን አንድ ነገር ሠርቼ ማለፍ ነው:: መጽሐፉን በማዘጋጅበት ወቅት ካልጠበቅሁት አቅጣጫ ብዙ ፈተናና ተስፋ አስቆራጭ ነገር ገጥሞኝ ነበር:: በዚህም ትዕግሥቴ፣ እምነቴ፣ ቅንነቴና ለጌታ ያለኝ ፍቅር ተፈትኖበታል:: ይህ ሁለተኛ ጊዜ ተሻሽሎና ታርሞ የተዘጋጀ እትም ሲሆን የመጀመሪያውን እትም በ1992 ዓ.ም. በሰኔ ወር ነበር አሳትሜ ያሠራጨሁት:: ነገር ግን በዚያኛው እትም ላይ ብዙ የቃላትና የጥቅስ ሥህተቶች ከመኖራቸውም በላይ አንዳንድ አባባሎችና ትምህርቶችም አላስፈላጊ ሆነው ስላገኘኋቸው አውጥቻቸዋለሁ:: በዚህ አጋጣሚ የመጀመሪያውን እትም በፍጥነት እንዳዘጋጅ ምክንያት ለሆነኝ ለወንድም ኤርምያስ ይርጉና ለሐረር አማኑኤል ህብረት አገልጋዮች መጽሐፏ መታሠቢያ ትሁንልኝ:: በመጽሐፏ ዝግጅት ለረዱኝና ለተባበሩኝ ለወንድም ኤልያስ አማረ፣ ለእህት ብዙነሽ ፋሪስ፣ ለእህት ስንታየሁ ዳኘ /አፍሪካ ማተሚያ ቤት/ እንዲሁም ለወንድሜ ደጀኔ አብርሃም ምሥጋናዬን በጌታ በኢየሱስ ስም አቀርባለሁ::

ይህችኛዋን መጽሐፍ ደግሞ በአገልግሎቴ እጅጉን ለተቀረጽኩባትና እስከ አሁንም ድረስ ለማገለግልባት ለተሃድሶ ክርስቲያኖች ህብረት መታሰቢያ ትሁንልኝ::

/መጽሐፍዋን ከሥልጠና ጋር ወይም መጽሐፍዋን ብቻ የሚፈልጉ ሁሉ በአድራሻው በኩል ያገኙናል::

እንኳ ሥቶ ላስጀመረኝ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለልኡል እግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን::

# መግቢያ

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ዓላማ እርሱን በሚገባ አውቀን ከእርሱ ባገኘነው የልጅነት ሥልጣንና መብት ሙሉ ለሙሉ እንድንጠቀምበት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ቤተክርስቲያን ባላት አቅምና ጉልበት ሁሉ ወደጌታ የሚመጡትን ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ለሰው ልጆች ያለውን እቅድ በሚገባ ማሳየት ይገባታል፡፡ ማንም ሰው እንደሚያውቀው ቁምነገሩ ልጅ መውለድ ሳይሆን ማሳደጉ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ የወለደቻቸውን ልጆች በእድላቸው እንዲያድጉ መተው የለባትም የዚህ የክትትል ትምህርት መሠረታዊው ሃሳብም ሰዎችን በክርስቶስ ትምህርት ስር ሰደው እንዲያድጉ፣ ተመሳሳይ የሆነ የመረዳት አንድነት እንዲኖራቸውና በቤተክርስቲያን ውስጥ ክርስቲያን ከመሆን አልፈው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር እንዲሆኑ ለመርዳት ነው፡፡

ይህ መፅሐፍ በተለይ የተዘጋጀው ሰዎችን በግላቸው ደቀመዝሙር ለማድረግ ፍላጎትና ጥማት ላላቸው አገልጋዮች ነው፡፡ ስለዚህም መጽሐፍ እንደ «የመምህሩ መምሪያ» አድርገን ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ በትምህርቱ ውስጥ ያሉ መግለጫዎችና የትምህርቱ ቅደም ተከተል አንድ አዲስ አማኝ በህይወቱ ሊገጥመው ከሚችለው ጥያቄዎች አንፃር የተዘጋጀ ነው፡፡

ስለዚህ አገልጋዩ ይህንን የክትትል ትምህርት ማሥተማሪያ መጽሐፍ ከመጠቀሙ በፊት በቂ ሥልጠና እንዲያገኝ ቢደረግ ውጤታማ እንደሚሆን እምነታችን ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ለአገልጋዩ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ትምህርቱ በክትትል ለአዲሱ አማኝ ለሚሠጠው አገልጋይ አማኞችን የመከታተል አሥፈላጊነትንና የመጽሐፉን አጠቃቀም ለማሥረዳት ሲሆን ትምህርቱ የሚሠጠው ለአገልጋዩ በሥልጠና ኘሮግራም ነው፡፡

**የቃል ጥናት ጥቅስ፡-** 2ኛ ጢሞ2÷2

*ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ፡፡*

## I. የክትትል አስፈላጊነት

በቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሆነውና እየሆነ ስላለው ነገር ልብ ብለን ብናስተውል አንድ አስገራሚና አሳዛኝ ነገር እናያለን፡፡ ብዙዎቻችን በየሰንበቱና ከዚያም ውጪ በምናደርጋቸው ስብሰባዎች ብዙ ሰዎች ወደጌታ ሲመጡ ወይንም ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ኢየሱስ ሲሰጡ ልባችን በደስታ የሚፈሰውን ያህል ደግሞ ብዙ ሰዎች ወደ ቀድሞው ሕይወታቸው ሲመለሱ እንመለከታለን፡፡ ለዚህም እያንዳንዳችን የራሳችንን የግምገማ ሃሳብ በመደገፍ 'ምክንያቱ ይሄ ነው' ለማለት ብንሞክርም ለዚህ አጠቃላይ መልስ ለመስጠት ግን አስቸጋሪ እንደሚሆንብን ሁላችንም የሚገባን ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ሰዎች ወደ ጌታ ቤት ከመጡ በኋላ ወደ ቀድሞው የሕይወታቸው ሥርዓት እንዲመለሱ ከሚያደርጋቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ቤተክርስቲያን ወይንም የክርስቶስ ማህበር ወደ እርሷ የመጡትን ሰዎች በሚገባ ያለመከታተሏ ውጤት መሆኑን የምንስማማበት ጉዳይ ነው፡፡

ሌላው ስለክትትል ስናነሳ የማናልፈው ቁም ነገር ሰዎች በጌታ ቤት ውስጥ ወራትና ዓመታት እያስቆጠሩ ነገር ግን በሕይወታቸው ይህ ነው የሚባል ለውጥ ወይም መንፈሳዊ ብስለት ያለማሳየታቸው ጉዳይ ሲሆን ለዚህም አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት ለምዕመኖቿ እንደ እድገታቸው መጠን እየመጠነችና እየተከታተለች መሠረታዊ ትምህርቶችን አለመስጠቷ ነው፡፡

ስለዚህ ወደጌታ የመጡትን አዳዲስ ሰዎች መከታተል ቤተክርስቲያን ከተሰጣት አደራ ዋነኛውና ለአፍታ እንኳ ልትዘነጋው የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡

## II. ስለክትትል የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት፣ ትዕዛዝና የተስፋ ቃል

1. የኢየሱስ ምሳሌነት

ኢየሱስ የመረጣቸውን እስከ መጨረሻው ድረስ በመከታተል በህይወቱ ምሳሌነቱን ትቶልን አልፏል:: ይልቁንም ከሞቱ በኋላ ለሦስት ዓመት ሙሉ ጊዜውን በመስጠት ቀንና ሌሊት ያስተማራቸው ሰዎች መበታተናቸው በሰው አይን ሲታይ ዋጋ ቢስና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ቢመስልም እርሱ ግን እስከ መጨረሻው ድረስ የተበታተኑትን ያሉበት ድረስ ሄዶ በመፈለግና እንደገና ከመጀመሪያ የነበረውን የልቡን ሃሳብ በመግለጥ አገልግሎቱን በተሳካ ሁኔታ ማከናወኑ ለእኛ ለአገልጋዮቹ ትልቅ ምሳሌ ሆኖን አልፏል:: ሉቃ24÷13-49, ዮሐ21÷19::

2. ትዕዛዝ

ጌታ ኢየሱስ ሥራው ሁሉ አከናውኖ ከዚህች ምድር ከፍ ከፍ ከማለቱ በፊት ለመረጣቸው፣ ለተከታተላቸውና 'ደቀመዛሙርቶቼ' ብሎ ለጠራቸው ሰዎች ታላቁን ተልዕኮ በሰጠበት ወቅት ሰዎች የምሥራቹን ቃል ከሰሙ በኋላ ክትትል እንደሚያስፈልጋቸው ተናግሯል:: ይህን የተናገረበትን የቃሉን መንፈስ ልብ ብለን ስናይ ሰዎችን መከታተል ወይም ደቀመዝሙር ማድረግ የጌታ ትዕዛዝ መሆኑን እንገነዘባለን:: ማቴ 28÷20::

3. የተስፋ ቃል

ለዚህ አገልግሎት ራሳቸውን ለሰጡ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ እስከዓለም ፍፃሜ ድረስ ከእነርሱ ጋር እንደሆነ በቃሉ አረጋግጧል:: በተጨማሪም አገልግሎቱን ለማከናወን የሚያስችለውን ኃይልና መንፈስ ቅዱስንም ለመረጣቸው አገልጋዮቹ እንደሚልክላቸው በሐዋ.ሥራ 1÷8 የተናገረ ሲሆን የገባውን የተስፋ ቃልም በሐዋ.ሥራ 2÷1 ላይ ሲፈጽመው እናያለን ማቴ 28÷20::

## III. ለክትትል ከሁሉም ይልቅ የተሻለው መንገድ

የጅማ የወንጌል ሥርጭት /ክሩሴድ/ ብዙ ሰዎችን ለውሳኔ እንደሚጋብዝ ከልምዳችን ያስተዋልነው ጉዳይ ሲሆን አንዴ ወስነው የመጡትን ሰዎች በተገቢው መንገድ ለመከታተል ያመችን ዘንድ አስቀድመን እቅድ ማዘጋጀት እንዳለብን እንገነዘባለን:: በዚህ ትምህርት አዘጋጆች ዕምነት ሰዎችን አንድ ለአንድ ማገልገል



ውጤታማነቱ ከሁሉም የተሻለ ነው:: ነገር ግን አስቀድሞ ከቤተክርስቲያን የሚጠበቀው ለዚህ አገልግሎት ራሳቸውን በሚገባ የሰጡ በቂ አገልጋዮችን ማዘጋጀት ነው:: አገልግሎቱ ቤተክርስቲያንን ውጤታማ ከማድረጉም በላይ ያሏትን አገልጋዮች ካላት ውስን የመድረክ /ፑልፒት/ አገልግሎት ሌላ በዚህ ውጤታማ በሆነ ተግባር በማሰማራት ብዙ ፍሬ እንድትሰበስብ ያስችላታል::

## IV. የቤተክርስቲያን ምሳሌነት

1. <u>በርናባስና ጳውሎስ ሐዋ፡ 9÷27</u>

ጳውሎስ ከሌሎች ሐዋርያት ሁሉ ዘግይቶ ጌታን የተቀበለ ሰው ነው:: ነገር ግን ከሌሎች አማኞች የሚለይበት አስደናቂ ታሪክም ያለው ሰው ነው:: ይህ ሰው ጌታ ኢየሱስንም ሆነ የእርሱን ተከታዮች የሚቃወምና እስከሞትም ድረሥ የሚያሳድድ ሰው ነበር:: /1ኛ ጢሞ1÷12-16:: ሐዋ7÷58 8÷3 9÷1-2/

በዚህም ምክንያት የጳውሎስን ለውጥ እውነተኛነት ዋነኛ ሐዋርያትን አማኞችንም አጠራጥሮ ነበር:: /ሐዋ 9÷10-17:: /ሐዋ.9÷20-26/

በዚህ ሁሉ መሐል በርናባስ ጳውሎስን ትዕግሥት በተሞላበት ሁኔታ መከታተሉ ከእርሱ ጋር ጊዜ ማሣለፉ አስደናቂ ነው:: ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡ አዳዲስ አማኞችን ያለፈ ታሪካቸውን በመመልከት ልናገላቸው እንደማይገባ ነው::

በምታገለግሉበት ህብረት ወይም ቤተክርስቲያን ሊለወጥ እንደማይችል አስባችሁት የነበረ ሰው ተለውጦ ያውቃል? ምን ተሠማችሁ? እስቲ ጥቂት ተወያዩባቸው::

2. <u>በርናባስና ማርቆስ ሐዋ:15÷36-38</u>

ከላይ በተጠቀሰው ክፍል ጳውሎስና በርናባስ በማርቆስ ምክንያት በመካከላቸው ልዩነት ሲፈጠር እንመለከታለን::

ይህ የሆነበት ምክንያት ምን ይመሥላችኋል? ይህንን ክፍል ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጥቅሶች ጋር አብራችሁ በማጥናት ተወያዩባቸው:: ሐዋ.13÷13:: 2ኛ ጢሞ. 4÷11

3. <u>ጽርስቅልና አቂላ አጵሎስን እንደተከታተሉት</u> ሐዋ 18÷24-28 በዚህኛው ምሳሌ ደግሞ ልባቸው በጌታ ፍቅር እየተቃጠለ ነገር ግን ተጨማሪ ዕውቀትና ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች እንዴት መከታተል እንዳለብን እናያለን፡፡

በክፍሉ የተጠቀሰውን ጥቅስ በማንበብ ተወያዩባቸው

- አጵሎስ ምን ዓይነት ዕውቀት ነበረው?
- ጵርስቅላና አቂላ ለአጵሎስ በተጨማሪ የገለጡለት ምን ዓይነት ዕውቀት ይመሥላችኋል?

## V. የክትትል ትምህርት ማሥተማሪያ መጽሐፉን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

1. ይህ የማስተማሪያ መጽሐፍ በቀላሉ የመጽሐፍ ቅዱስን የደህንነት ዕቅድ ለአዲሱ አማኝ በጥናት በተደገፈ ሁኔታ እንዴት እንደምታስረዳው ያሳይሃል፡፡ ስለዚህ አስቀድመህ በዚህ መጽሐፍ ከማገልገልህ በፊት ስለ ትምህርቱ በቂ የሆነ ስልጠና ብትወስድ ትምህርቱን የማስተማሩን ዘዴ በሚገባ ልትረዳው ትችላለህ፡፡
2. በየትምህርቶቹ መግቢያ ላይ ያሉት ማብራሪያዎች ከሥልጠናው በኋላ ስለትምህርቱ ዓላማ ሁልጊዜ ግንዛቤህን ለማዳበር የሚረዱህ ስለሆነ በየጊዜው ብታነባቸው ይጠቅሙሃል፡፡
3. አንዳንድ አባባሎችንና ጥቅሶችን በተደጋጋሚ በትምርህርቱ ውስጥ የምታገኛቸው ነገሩ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነጥብ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ይህም አዲሱን አማኝ ስለነገሩ እርግጠኛነት ከተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከተው ይረዳዋልና ይሰለቸዋል ብለህ አትስጋ፡፡ ነገር ግን አማኙ ስለነገሩ በሚገባ ተረድቷል ብለህ በሚሰማህ ጊዜ ትምህርቱን ልታልፈው ወይንም ላታነሳው ትችላለህ፡፡
4. በእያንዳንዱ የትምህርት ጊዜ ከ30-40 ደቂቃ ብቻ ማገልገሉ ከሁሉም የተመረጠ ሰዓት ሊሆን ይችላል፡፡
5. ልብ በል!

   5.1. በዚህ መጽሐፍ ላይ የተፃፉት ጽሑፎች ወይንም ትምህርቶች መሠረታዊውን ሃሳብ ለመጠቆም የቀረቡ እንጂ ተጨማሪ ሃሳቦችን እንዳትናገር የሚያግዱ አይደሉም፡፡ በየጊዜው



ለማገልገል በምትዘጋጅበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራህ ራስህን አሳልፈህ መስጠት ይጠበቅብሃል፡፡

   5.2. አንዳንድ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ **የእግዚአብሔር መንፈስ ይህንን** ትምህርት አቁመህ ሌላ ነገር እንድ**ታገለግለው ሊያዝህም** እንደሚችል አስቀድመህ ተረዳ፡፡ መንፈስ **ቅዱስ** ለምታገለግለው ሰው ከተዘጋጀህበት ትምህርት ውጪ ሌላ መልዕክት እንድትነግረው በልብህ ከሞላ የግድ 'ይህንን ነው ማገልገል ያለብኝ' ብለህ አታስብ፡፡

   5.3. በዚህ የክትትል ትምህርት መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ጥቅሶችና ማብራሪያዎች ውጪ ሌሎች ምሳሌዎችና ማብራሪያዎችን መጠቀም የተሻለ መስሎ ከተሰማህ ይህን ከማድረግ አትቆጠብ፡፡

   5.4. ትምህርቱን 'አውቀዋለሁ' ብለህ በጌታ ፊት ከመፀለይና ቃሉን ከማጥናት ራስህን ፈፅመህ አታዘናጋ፡፡ በእያንዳንዱ አገልግሎትህ ስለምታገለግለው ሰውና ስለምታስተምረው ትምህርት ራስህን በፀሎት ለጌታ አቅርብ፡፡

## VI. <u>ተጠንቀቅ</u>

አዲሱ አማኝ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ያንተን ህይወት ማንበብ ይቀለዋል፡፡ ስለዚህ በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽህናም ለሚያምኑት ሁሉ ምሳሌ ሁን እንጂ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው፡፡/1ኛ ጢሞ 4÷11/

## VII. <u>ተጨማሪ መግለጫ</u>

እነዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አሳቦች ትምህርቱን ለሚሠጠው አገልጋይ ተጨማሪ እገዛ እንደሚሠጡት ሥለታመነበት አሥፈላጊ በሆነ ጊዜ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

1. <u>የቃል ጥናት ጥቅስ</u>

   ትምህርቱን የሚከታተለው /አዲሱ አማኝ/ በተቻለ መጠን በቃሉ ለመያዝ እንዲያጠናው ቢደረግ ትምህርቱን ከህይወቱ ጋር እንዲዋሃድ የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል በተጨማሪም አማኙ መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ እንዲያጠና ያደፋፍረዋል፡፡

2. <u>ለአገልጋዩ</u>

   ይህ ቃል በተጠቀሠበት የትምህርት ክፍል ሁሉ አገልጋዩ ሥለ ትምህርቱ የበለጠ ትኩረት እንዲያደርግ ሲያሥፈልግ ነው፡፡

3. <u>ስሰላዊ መግለጫዎች</u>

በአዲሱ አማኝ ውስጥ በቀላሉ የማይረሱ ትውስታዎችን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ በታመነበት ሥፍራ እንዲኖሩ ተደርጓል። ነገር ግን ፍጹም የሆነ ትርጉም ባይሠጡህ ወይም ትርጉማቸው ጨርሶ ግልጽ ባይሆንልህ መጨነቅ አይገባህም።

4. <u>የትምህርቱ ዓላማ</u>

ይህ በእያንዳንዱ ትምህርት መግቢያ ላይ ሥለ ትምህርቱ ዓላማ በአገልጋዩና በተገልጋዩ ትኩረት እንዲሠጥበት የተቀመጠ ክፍል ነው።

5. <u>የምዘና ጥያቄ</u>

ሁልጊዜ ከትምህርቱ በኋላ በጽሑፍ እንዲያመጣልህ አድርግ ምናልባት ግን በዚህ የሚጨነቅና ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ብዙ አታሥጨንቀው።



# <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የመጀመሪያ ደረጃ የደህንነት ትምህርት</u>

ለአገልጋዩ
<u>የምዕራፍ ክፍለ ትምህርቶች ዓላማ</u>

1. በዚህ ምዕራፍ ሰባት ትምህርቶችን ታገኛለህ ይህ ምዕራፍ ስለደህንነት እርግጠኛነት በቀላል ቋንቋና በተወሠነ ጥቅሶች የምታሥረዳበት ክፍለ ትምህርት ነው።

2. ትምህርቱ የመጀመሪያ ትምህርት እንደመሆኑ መጠን ለአዲሱ አማኝ ውስብስብ በማይሆንበት መንገድ ልታሥተምረው ይገባሃል።

3. አማኙ አዲስ እንደመሆኑ መጠን በእያንዳንዱ ንዑስ የትምህርት ርዕሥ ላይ የምትጠቅሰው ጥቅስ ከአንድ ወይም ከሁለት ባይበልጥ ጥሩ ነው።

4. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት ትምህርቶች በድጋሚ በሥፋት ልትሠጠው የምትችልበትን ክፍለ ትምህርት በቀጣዮቹ ምዕራፎች ላይ እንደምታገኘው አትዘንጋ።

5. ትምህርቱ በአጭሩ ወደ ቤተክርስቲያን ህብረት የመጣውን አዲሱን አማኝ ደህንነቱን እርግጠኛ ማድረግን፣ በጌታ እንዲያድግ መርዳትን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግና መንፈስ ቅዱስን ማወቅ የሚችልበትን ጠቃሚ አሳቦች አካቷል።

ይህን ትምህርት እስከትጨርስ ተማሪህ ከአንተ ጋር እንዲቆይ የእግዚአብሔር እርዳታ እንዲሆንልህ ፀልይ!

# ምዕራፍ ሁለት

## ትምህርት አንድ

## የወንጌሉ ቃል

❖ የትምህርቱ ዓላማ

በተለያየ መንገድ ሰዎች የወንጌል ቃል ወይም መልካሙን ዜና ሰምተው ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣት ህብረትን ሊያደርጉ ይችላሉ:: ነገር ግን በሠሙት ቃል የደህንነት መንገድን ምን ያህል እንደተረዱት እርግጠኛ ለመሆን አስቸጋሪ ነው::

ስለዚህ የዚህ ትምህርት ዓላማ በተለያየ መንገድ ወንጌልን ሰምተው በጌታ ያመኑትን ሰዎች የተመሠከረላቸውን እውነት በትምህርት መልክ በማቅረብ እርግጠኛ ሆነው እንዲቀበሉትና ለሚቀጥሉት ትምህርቶች የፀና መሠረት ለመመሥረት ታሥቦ የተዘጋጀ ነው::

1. ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነቱን እንዲያውቁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: 1ኛ ጢሞ 2÷3

2. ሰው ሁሉ ሃጢያተኛ ነው:: ሮሜ 3÷23

   «ሁሉ ኃጢያትን ሰርተዋል
   የእግዚአብሔርም ክብር ጎሏቸዋል::»

3. የኃጢያተኛ ፍርዱ የዘለዓለም ሞት ነው:: ሮሜ 6÷23

   «የሀጢያት ደሞዝ ሞት ነውና»

4. በክርስቶስ በማመን እንዲያው በፀጋው መዳን ይቻላል:: ዩሐ3÷16

   «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሠጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና::»

5. አለማመን ፍርድ አለው:: ዩሐ 3÷17

   «በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ሥም ስላለመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል::»



6. በክርስቶስ በማመን ከሞት ወደ ሕይወት መሻገር ይቻላል:: ዮሐ5÷24

   «ቃሌን የሚያከብር የላከኝንም የሚያምን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም::»

7. ለአገልጋዩ

   ❖ እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን መጠይቆች ወይም ሌላ በቃላ በዕለቱ አዲሱን አማኝ በመጠየቅ ሥለ ደህንነቱ ያለውን ዕውቀት ተረዳ::

   ሀ/ እግዚአብሔር የሚወድህ ይመሥልሃል?

   ለ/ እግዚአብሔር እንዳዳነህ እርግጠኛ ነህ?
   /እርግጠኛ ካልሆነ ሳትታክትና ሳትሰለች አብረኸው ጊዜ አጥፋ/

   ሐ/ አሁን እንድፀልይልህ ፈቃደኛ ነህ?
   /ፈቃደኛ ከሆነ በፀሎት እርዳው/



ስዕል ፩

# ትምህርት ሁለት

## የምሥራች

**የትምህርቱ ዓላማ:**

አዲሱ አማኝ በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘው ደህንነት ከሁሉ የሚበልጥ መልካም ዜና ወይም የምሥራች እንደሆነ ለማሥረዳት:
የቃል ጥናት ጥቅስ:- ሉቃ 2÷10-11

«እነሆ ለህዝቡ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ:: ዛሬ በዳዊት ከተማ መድሃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና::»

◆ <u>የምሥራች</u>

1. የምሥራች ማለት መልካም ወሬ ወይም ጥሩ ዜና ማለት ነው፣

2. የምሥራች ለሰሚው መልካም ዜና የሚሆነው ሰሚው ለሚሰማው ባለው የልብ መዘጋጀት ወይም ናፍቆት ነው፣

3. አንዳንዴ የምሥራች ብለን ለሌሎች የምንናገረው ነገር ለሚዎችን ሊያሳዝን ወይም ሊያስቆጣ ይችላል::

   ምሳሌ 2ኛ ሳሙ 18÷19-33

   <u>ለአገልጋዩ:</u>

   በዚህ ክፍል ላይ ያለውን ታሪክ ተርክለት::

4. *ለሰው ሁሉ የሚሆን የምሥራች በዚህ ምድር ላይ የለም:: እስቲ እነዚህን ነገሮች ልብ በል፤ ሥለ ጦርነትና ስፖርት ወይም ስለክብርና ዝና በሰዎች የሚነገር የምሥራች በአንዱ መጎዳት ሐዘንና ማጣት እንዲሁም ውርደትና መጉደል ላይ የተመሠረተ ሥለሚሆን የምሥራችነቱ ለአንዱ ወገን ብቻ ነው:: ሌላው ደግሞ አንዱን አሥፈንድቆ የምሥራች ወይም መልካም ዜና የሆነለት ለሌላው ሰሜት የማይሠጥ ሊሆን ይችላል::*

5. የኢየሱስ መወለድ ሞትና ትንሣኤ ግን ለሰው ሁሉ የሚሆን የምሥራች ነው:: ሉቃ 2÷10-11



6. ሰው በዚህ ዓለም ብዙ መልካም ወሬዎችን ወይም በየዕለቱ ብዙ የምሥራቾች ቢኖሩት፤ ነገር ግን የክርስቶስን የምሥራችነትን ባይሠማ ምን ይጠቅመዋል::
   ማቴ.16÷26

   *<u>ለአገልጋዩ:</u> አሥቀድመህ አሳቡን በቃሉ እንዲገልጥልህ ካደረግህ በኋላ ጥቅሱን አንብብለትና አስረዳው::*

   «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል ወይሥ ሰው ሥለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሠጣል?»

   ◆ *ሐብታም ብትሆን ድሃ፣ የተማርክ ብትሆን ያልተማርክ ዝነኛ ብትሆን ማንም የማያውቅህ፣ በሽተኛ ብትሆን ጤነኛ፣ ወንድ ብትሆን ሴት፣ የተከበርክ ብትሆን የተዋረድክ፣ ትንሽ ብትሆን ትልቅ፣ ነጭ ብትሆን ጥቁር ... ብቻ በየትኛውም ሁኔታና ኑሮ ያለህ እንኳ ብትሆን በዚህም ምድር ላይ በህይወት እስከኖርክ ድረስ ይህ የምሥራች ቃል ያስፈልግሃል::*

7. አንተ ግን ይህ የምሥራች ደርሶሃልና ዕድለኛ ነህ እንኳን ደስ ያለህ!

   *<u>ለአገልጋዩ:</u> ስለዚህ በህይወቱ ሥላገኘው አዲስ ነገር እግዚአብሔርን እንዲያመሠግን በፀሎት እርዳው::*

## <u>የምዘና ጥያቄ አንድ:</u>

1. የምሥራች ምን ማለት ነው?

2. ለሁሉ የሚሆን የምሥራች አለ? ካለ እንዴት ሆኖ?

3. በሕይወት ዘመንህ ከሰማሃቸው የምሥራቾች ሁሉ ብልጫ ያለው የትኛው ነው? ለምን ?

4. በዚህ ትምህርት ለራስህ ምን አገኘህ?

# ትምህርት ሦስት

# በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን

**የትምህርቱ ዓላማ:**

**አማኙን በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ ለማሥረዳት::**

**የቃል ጥናት ጥቅስ:**
**ሮሜ 10÷17**

**«እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው::»**

***ለአገልጋዩ:-***

***ለሚማረው ትምህርት ሁሉ መሠረታዊ እምነቱን በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንዲያደርግ አሥረግጠህ ንገረው::***

- **በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት**

1. **እርሱ ስለእኔ ኃጢያት ምትክ ሆኖ ሞተልኝ ማለት ነው:: ይህም**

    **እኔ ኃጢያተኛ ነኝ፣ እርሱ ፃድቅ ነው**
    **እኔ ወንጀለኛ ነኝ፣ እርሱ ንፁህ ነው**

    **ነገር ግን**

    **እኔ መቀጣት ሲገባኝ ቅጣቴን ተቀጣልኝ**
    **እኔ መሞት ሲገባኝ እርሱ ሞቴን ሞተልኝ ወ.ዘ.ተ**

    **ብሎ እንደማመን ነው::**

***ለአገልጋዩ:-***

***ክርስቶስ በበርባን ምትክ መሰቀሉንና ሰዎችም ከኢየሱስ ይልቅ በርባንን መውደዳቸውን ለምታገለግለው ሰው በሚገባው መልኩ አሥረዳው::***






ስዕል ፬

2. **ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢያት የሚያድን ብቸኛ አዳኝ መሆኑን ማመን ማለት ነው:: ሐዋ 4÷12**

3. **ወደ እግዚአብሔር አብ የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ መሆኑን ማመን ማለት ነው:: ዮሐ 14÷6**

4. **ኢየሱስ ጌታ ነው ብሎ ለጌትነቱ መገዛትም ነው:: ሮሜ 10÷9**

## የምዘና ጥያቄ ሁለት:

**ክፍል ሁለት**

1. **በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ማለት ምን ማለት ነው?**

2. **ኢየሱስ ከኃጢያት የሚያድን ብቸኛ መንገድ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?**

3. **ኢየሱስ ጌታ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?**

4. **ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ ነው ሥንል ምን ማለታችን ነው?**

# ትምህርት አራት

## በክርስቶስ የማመን ዋስትና

ብዙ ሰዎች በአንድ ነገር ላይ እምነት እንዲኖራቸውና ከሃሳብ ከሥጋት ነፃ እንዲሆኑ ዋስትና ይጠይቃሉ። ወይም ስለ ወደፊት ኑሯቸው አስተማማኝነት አሁን ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ሳሉ እርግጠኛ ለማድረግና ዋስትና ለማግኘት የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ስለዚህም አንድ በክርስቶስ የሚያምን ሰው እምነቱ ስለሚያስገኝለት ዋሥትና ቢጠይቅ የሚያሥደንቅ አይደለም።

የትምህርቱ ዓላማ

ክርስቶስ አዳኙ እንደሆነ የተቀበለውን አማኝ በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት በህይወቱ የተከናወኑትን የእግዚአብሔር ሥራዎች እንዲያስተውልና ከዚህ በኋላ በቀረለት ዘመኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ተረድቶ በነፃነት የሚኖርበትን ኑሮ ለማመላከት ነው።

*የቃል ጥናት ጥቅስ*

> *እግዚአብሔርን በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ህይወትን ሰጠን። ኤፌ 2÷4-5*

1. እግዚአብሔር ተቀብሎሃል። ዮሐ 6÷37-38

   ሀ. ወደክርስቶስ የመጣኸው እግዚአብሔር ስለአዳነህ ነው
   ለ. እግዚአብሔር ስለተቀበለህ ለዘላለም አይተውህም
   ሐ. ይህም የእግዚአብሔር የዘላለም ፈቃድና እቅድ ነው።

2. ኃጢያትህ ይቅር ተብሏል። ቆላ 2÷13

   በበደልህ /በኃጢያትህ/ ምክንያት ሙት ነበርክ ነገር ግን ኃጢያትህ ሙሉ ለሙሉ ተወግዷል።

3. የዘላለም ህይወት አግኝተሃል። 1ኛዮሐ 5÷11-13

   ሀ. የዘላለም ህይወት የሰጠህ እግዚአብሔር ነው
   ለ. ይህም ህይወት ያለው በክርስቶስ ነው
   ሐ. ይህን ህይወት ያገኘኸው ኢየሱስ በአንተ ውስጥ በመኖሩ ነው።



4. አንተ በእግዚአብሔር እግዚአብሔርም በአንተ ውስጥ ይኖራል። 1ኛ ዮሐ4÷15

   ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በማመንህ ይሄ ሆኖልሃል።

5. ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ተጠርተሃል። 1ኛጴጥ 2:9

   ሀ. ቀድሞ በጨለማ ትኖር ነበር /የቀደመው ህይወትህ የጨለማ ህይወት ነበር/፡

   ለ. ክርስቶስ ለዓለም ብርሃን ሆኖ ወደዚህ ዓለም መጥቷል። ዮሐ 1÷5, ዮሐ 1÷9

   ሐ. ያለክርስቶስ የሚኖር በጨለማ ውስጥ ይኖራል። ዮሐ 12÷46

   መ. አንተ ግን በክርስቶስ በመሆንህ በብርሀን ነህ።

6. የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል። ዮሐ 1÷12-13

   ሀ. የእግዚአብሔር ልጅ የሆንከው ክርስቶስን በመቀበልህና በማመንህ ነው

   ለ. የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ስልጣንና /መብትን/ አግኝተሃል

   ሐ. ይህንም ልጅነት ያገኘኸው በተፈጥሮአዊው ውልደትህ ሳይሆን በመንፈስ ዳግመኛ ከእግዚአብሔር በመወለድህ ያገኘኸው ነው።

   *<u>ለአገልጋዩ፡-</u> ዳግመኛ መወለድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በደንብ ለማስረዳት የሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሦስትን /የኒቆዲሞስንና የኢየሱስ ንግግር/ መጠቀም ትምህርቱን የበለጠ ግልጽ ያደርግለታል።*

7. አዲስ ፍጥረት ሆነሃል። 2ኛ ቆሮ 5÷17

   ሀ. በክርስቶስ በማመንህ ያገኘኸው ነው
   ለ. አሮጌው ማንነትህ አልፎ አዲስ ሰው ሆነሃል

8. በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ብቃትን አግኝተሃል

   ሀ. ወደ እግዚአብሔር የምትቀርብበትን ድፍረት ያገኘኸው በክርስቶስ ነው። ኤፌ 2÷18

ለ. ከክርስቶስ ውጪ በራሴ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ብቃት አለኝ ለማለት ቀርቶ ለማሰብም እንኳ ብቃት የለህም።
2ኛ ቆሮ 3÷4-5

## <u>የምዘና ጥያቄ ሦስት</u>

1. ደህንነት ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. እግዚአብሔር በኢየሱስ ከሰጠህ የደህንነት ዋስትና መሐል ስድስቱን ግለጽ፡
3. ከተሰጡህ ዋስትናዎች የበለጠ ልብህን የሚነካው የትኛው ነው? ለምን ?
4. በዚህ ክፍል ያጠናኸው የቃል ጥናት ጥቅስ ፃፍ።

# <u>ትምህርት አምስት</u>

## <u>በክርስቶስ ትምህርት ማደግ</u>

ህፃን ሲወለድ ወላጆችን ደስ እንደሚያሰኛቸው ሁሉ ከተወለደ በኋላ ደግሞ ማደግ እንደሚገባው ወቅቱን ጠብቆ ሲያድግና ለውጥ ሲያሳይ መመልከት ለወላጆቹ ትልቅ እርካታ ነው። በዚሁ አንፃር ለወላጆች ትልቁ የልብ ስብራት የሚሆነው ከተወለዱበት ጊዜ የዘገየ ወይም አዝጋሚ እድገት የኖራቸው እንደሆን ወይም ጭራሽኑ እድገት ያቆሙ እንደሆነ ነው። ያ ልጅ ለአባቱና ለእናቱ በመወለዱ ካገኙት ደስታ ይልቅ የከፋ ሐዘን ውስጥ ይጨምራቸዋል። ይህን ስናይ ዕድገት ለተወለደ ሁሉ ምን ያህል አስፈላጊ ነገር እንደሆነ እንገነዘባለን።

*'ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለ ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም። ምሳሌ 22÷6'*

በዚህም *መሠረት* ስለዕድገት ስናስብ ልክ *ሥጋዊ* እድገት እንዳለ ሁሉ *መንፈሳዊ* እድገት እንዳለ፣ *ሥጋዊ* አለማደግ እንዳለ ሁሉ *መንፈሳዊ* አለማደግ እንደሚኖር ማወቅ ይገባናል። ብዙ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን ካወቁ ብዙ ዓመት ቢቆጥሩም፣ መንፈሳዊ ዕድገታቸው ግን በዕድሜ መጠናቸው ልክ ሳያድግ አንድ ቦታ ተገድቦ ወይም አዝጋሚ ሆኖ ይታያል። በዚህም



ዘውትር ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ሕዝብ የልብ ሐዘን እንደሆኑ ይኖራሉ። ይህ እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። በዚህ ትምህርት በመንፈሳዊ ዕድሜአችን ልክ ማደግ እንድንችል የሚረዱንን መሠረታዊ ሐሳቦችን እናያለን።

**የትምህርቱ ዓላማ**

አዲስ ህይወት ያገኘውን አማኝ በመንፈሳዊ ህይወቱ ማደግ የሚችልበትን መንገድ በመጠቆም በህይወቱ እንዲለማመዳቸው ለማስተማር ነው።

*የቃል ጥናት ጥቅስ*

*«ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህንን አስብ ይህንን አዘውትር። 1ኛ ጢሞ 4:15»*

## <u>ክፍል አንድ</u>

1. መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ



ስዕል፡ ፲

1.1. መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ጥቅም

ሀ. ለእውቀት ሆሴ 6÷6

1/ ስለ እግዚአብሔር
2/ ስለ ራስህ
3/ ስለ ሌሎች ሰዎች
4/ ስለ ሌሎች ፍጥረታት እንድታውቅ ይረዳሃል

ለ. የታደሰ አእምሮ ለመያዝ እንድትችል ይረዳሃል። ያዕ 1÷21 እና ሮሜ 12÷2

ሐ. የህይወት መመሪያ ለማግኘት ይጠቅምሃል። 2ኛ ጢሞ 3÷16

<u>ለአገልጋዩ፡</u>

*ስለእነዚህ ነገሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ዕውቀት ከሌለው ወደጥፋት /ስህተት/ ሊሄድ ስለሚችል ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ አብራራለት።*

1.2. በመጽሐፍ ቅድስ ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል ከተመሰለባቸው ጥቂቶቹ

ሀ/ ብርሃን መዝ. 119÷105
ለ/ ምግብ 1ኛ ጴጥ2÷2
ሐ/ ሰይፍ ኤፌ. 6÷17
መ/ ዘር ሉቃ 8÷11-15

*ለአገል.ጋዩ:*

*ከእነዚህ ውጪ ሌሎች ብዙ ምሳሌዎች እንዳሉ ሳትዘነጋ ተጠቀምባቸው*

1.3. ሳነበብከውና ለተማርከው የእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ ይገባሃል:: ያዕ 1÷22, 1ኛ ሳሙ 15÷22

## 2. ፀሎት

### 2.1 የፀሎት ትርጉም

ፀሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር በአንድ በተወሠነ ርዕስ ላይ መነጋገር ማለት ነው::

*ለአገል.ጋዩ:*

*ፀሎት የአንድ ወገን /የሰው/ ብቻ ንግግር እንዳልሆነ አስረዳው::*

### 2.2 የፀሎት አስፈላጊነት

ሀ. የሚያስፈልገንን ከእግዚአብሔር ለመቀበል:: ማቴ. 7÷7
ለ. የሚያስጨንቀንን ነገር ለእግዚአብሔር በመንገር ከእግዚአብሔር እርዳታ ለማግኘት:: 1ኛ ጴጥ 5÷7
ሐ. ወደ ፈተና ላለመግባት:: ማቴ 26÷41

### 2.3 ውጤታማ ፀሎት ለመጸለይ

ሀ. በእምነት ፀልይ:: ማቴ. 17÷20
ለ. በንፁህ ልብ ፀልይ:: መዝ 66÷18-20 ማቴ 5÷23-24
ሐ. በቅንነት ፀልይ:: መዝ 7÷10
መ. ፀሎትህን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አድርግ:: ዮሐ 14÷14

### 2.4 ፀሎት የሚያካትታቸው ዋና ዋና ነገሮች

ሀ. ልመና - ስለግል ህይወት መዝ 54÷1-7
ለ. ምልጃ - ስለሌሎች ሰዎች ኤፌ. 1÷15-19
ሐ. ምስጋና - ስለሁሉ ነገር መዝ 50÷23
መ. ውዳሴ - እግዚአብሔርን ስለእግዚአብሔርነቱ፣ /ስለሁሉን ቻይነቱ፣ ስለአምላክነቱ፣



ስለታላቅነቱ ........ እያሰብክ አወድሰው፡፡ መዝ 105÷1-3/
ሠ. ንስሃ - በዕለቱ ከቃሉ ውጪ የፈጸምከው ስህተት ካለ ፈጥነህ በመናዘዝ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማማ:: ማቴ 26÷75

*ለአገል.ጋዩ*

*ስለንስሃ በሚቀጥለው ትምህርት ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለመስጠት እንደተዘጋጀህ አስረዳው::*

## 3. በእግዚአብሔር መታመን

3.1 እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይጠብቅሃል:: መዝ. /121/÷7
3.2 እግዚአብሔር ስለ አንተ ያስባል:: 1ኛ ጴጥ 5÷7

ሀ. በእግዚአብሔር ብቻ ታመን
ለ. እግዚአብሔርን ብቻ ተስፋ አድርግ
ሐ. የሚያስጨንቅህን ነገር ለእግዚአብሔር ንገር እንጂ አንተ መጨነቅ የለብህም::

3.3 እግዚአብሔር ስለአንተ ይዋጋል:: ዘፀ.14÷14:: ዘፀ15÷3

3.4 በእርሱ ከአሸናፊዎች ሁሉ ትበልጣለህ:: ሮሜ 8÷37

*ለአገል.ጋዩ*

*ከዚህ በታች ያሉት ሁለት ነጥቦች ከላይ እንዳሉት ሦስት ነጥቦች ከእድገት አንፃር የግድ አስፈላጊ ናቸው ብሎ መደምደም ባይቻልም ለአማኙ የግል ህይወት እድገት ያላቸው ጠቀሜታ ግን በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: አንዳንዴ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ይህንን ለማድረግ ባይችል ለማደግ የግድ አስፈላጊ የሆነ ነገር እንደጎደለው መስሎ እንዳይሰማው አስረግጠህ ንገረው::*

## ክፍል ሁለት

4. ከአንተ በፊት ጌታ ኢየሱስን ካወቁና ከተረዱ ሰዎች ጋር የጠበቀ ህብረት ይኑርህ:: 2ኛ ጢሞ 2÷22

4.1 በንፁህ ፍቅርና በወንድምነት ቅረባቸው
4.2 በሰላም ኑር
4.3 ሕይወታቸው እንደቃሉ ካልሆነ አትከተላቸው
4.4 ከክርክርና ከጥልና ከጠብ ራቅ
4.5 ጌታ ኢየሱስን ከማወቅህ በፊት ከነበሩህ ጓደኞችህ የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘው መሠረት ጓደኝነትህን

በልክ አድርገው፡፡ ነገር ግን አሁን ከጌታ ጋር ሳለህ ጉዞ እንቅፋት የሚሆኑብህ ከመሰለህ በፍቅርና በትህትና ለመራቅ ሞክር በማናቸውም ክፉ ሥራቸው አትተባበራቸው፡፡ 1ኛ ቆሮ 15÷33

5. በአመንክበት ሳታፍር ስለአዳኝነቱ ተናገር፡፡ ሮሜ 1÷16

*ለአገል ጋዩ፡*

*አንድ ሰው በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት ብዙ ተቃውሞና ክርክር ይገጥመዋል፡፡ ይህም ባመነው ነገር ላይ ጥርጣሬን በመዝራት በእድገቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለዚህም ይህንን ጥናት ስታስጠናው በፊልጶስና በናትናኤል መካከል የነበረውን ልዩነትና የፊልጶስን ጠንካራ ዕምነት ማሳየት ይጠበቅብሃል፡፡*

የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት

ዮሐ 1÷44-52

5.1 የምታውቀውንና አንተ የተለወጥክበትን ቃል ብቻ ተናገር፡፡ ዮሐ 1÷46
5.2 አንተ የማታውቀውን ጥያቄ ቢጠይቅህ አትደናገጥ፡፡ ዮሐ 1÷47
5.3 ጌታ ኢየሱስን ማንም በጥያቄ ሊረታው እንደማይችል እመን፡፡ ዮሐ 1÷48-49
5.4 ጌታ ኢየሱስ የሰዎችን ጥያቄ በአጥጋቢ ሁኔታ እንደሚመልስና ሕይወታቸውንም እንደሚለውጥ እመን፡፡ ዮሐ 1÷50

## የምዘና ጥያቄ አራት

1. መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ለምን ይጠቅማል?
2. የእግዚአብሔር ቃል ከተመሰለባቸው መሐል አራቱን ፃፍ፡
3. ፀሎት የሚያስፈልገው ለምንድነው?
4. ውጤታማ የሆነ ፀሎት መፀለይ የሚቻለው እንዴት ነው?
5. በፀሎት ከሚካተቱ ነገሮች መሃል ጥቂቶቹን ጥቀስ፡
6. በእግዚአብሔር መታመን ማለት ምን ማለት ነው?
7. ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ሕብረት ማድረግ ከእድገት አንፃር ያለው ጠቀሜታን አስረዳ፡
8. ወንጌል የማያሳፍረው ለምንድነው?
9. በቃልህ ያጠናኸውን ዋነኛ ጥቅስ ፃፍ?



# ትምህርት ስድስት

# ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ

ፍጥረትን ልብ ብሉ ሳስተዋለ፣ እነዚህን ሁሉ አስደናቂ ፍጥረታትን በፈጠረው በእግዚአብሔር መደነቁ አይቀርም፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በላይ አስደናቂው ነገር እነዚህ ሁሉ ድንቅ ፍጥረታት ለሰው ልጅ የተፈጠሩ መሆናቸው ነው፡፡ ሰው ደግሞ የተፈጠረው ለእግዚአብሔር ክብር ሲሆን በፍጥረቱ የመጀመሪያ ወቅቶች ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ህብረት እንደነበረው ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ነገር ግን ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ ስቶ እንደ ፈጠረው እግዚአብሔር ሊሆን እንደሚችል የተናገረውን የሰይጣንን ድምፅ በሰማና በታዘዘ ጊዜ እንዲሁም አትብላ የተባለውን የዛፍ ፍሬ ሕግ ተላልፎ በበላበት ወቅት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ድንቅ ህብረት ሊያበላሽ ቻለ፡፡ በዚህም ምክንያትም ከተፈጠረበት ዓላማ ውጪ የሆነውን ኑሮ መኖር ግዴታው ሆነ፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር ምንም እንኳ የሰው ልጅ በአመፁ ክብሩን ቢያጣም እርሱ የቀጠረው ቀን ሲደርስ ከሴት የተወለደ ልጁን ወደምድር ላከው (ገላ4÷4)፡፡ እርሱንም እግዚአብሔር ሲመሰከተው 'የምወደው ልጇ እርሱ ነው እርሱን ስሙት' ሲል ልቡ በልጁ እንዳረፈ መሰከረለት፡፡ ልጁም በመስቀል ላይ ስለ ሰዎች ኃጢያት የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ነዶ የሰውን ልጆች ግን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ፡፡

በዚህ ትምህርታችን ስለእግዚአብሔርና ሰው ህብረት፣ ስለሰው ኃጢያት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ህብረት እንደገና ለመመስረት የከፈለውን ዋጋና ስለ ሰው በክርስቶስ መጽደቅ እንመለከታለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህንን ህብረት ዕለት ዕለት እንዴት እንደምናጸናም እንማራለን፡፡

## የትምህርቱ ዓላማ

በኃጢያት ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን መለያየት እግዚአብሔር አንድ ልጁን በመላክ ስላስተካከለው በክርስቶስ በኩል መታረቅን ያገኘው አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የማድረግ ብቃት እንዳለው በማረጋገጥ ህብረት እንዲያደርግ ለማደፋፈር ነው።

## የቃል ጥናት ጥቅስ

ህብረታችን ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው። 1ኛ ዮሐ 1÷3-4

## I. የእግዚአብሔርና የሰው ህብረት

1. ሰውና እግዚአብሔር በሰው ፍጥረት መጀመሪያ

   1.1. ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጥሮ ነበር። ዘፍ 1÷26
   1.2. በምድር ላይ ገዢ እርሱ ብቻ ነበር። ዘፍ 1÷26
   1.3. እግዚአብሔር ለሰው ከሰው ይልቅ ያስብለት ነበር። ዘፍ 2÷18
   1.4. ለሰው በሰጠው ስልጣንና ሰውም በሚሰራው ሥራ ሁሉ ደስተኛ ነበር። ዘፍ 2÷19

2. የሰው ውድቀት

   ሰው እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ ባለማክበሩ /ኃጢያትን በመስራቱ/ ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው አስደናቂ ህብረት ተበላሸ። ዘፍ 3÷6

3. የኃጢያት ውጤት

   5.1 ከኤደን ገነት ተባረረ። ዘፍ 3÷23
   5.2 ምድር ከሰው ኃጢያት የተነሳ የተረገመች ሆነች። ዘፍ 3÷17
   5.3 በወዙ ጥሮ ግሮ እንዲኖር ተፈረደበት። ዘፍ 3÷19
   5.4 የእግዚአብሔር ክብር የጎደለው ሆነ። ሮሜ 3÷23
   5.5 ለኃጢያቱም ደመወዝ /ዋጋ/ ሞት ተፈረደበት። ዘፍ 3÷19 ሮሜ 6÷23

*ለአገልጋዩ፦*

*የሥጋዊና የመንፈሳዊ ሞትን ትርጉም ለያይተህ አስረዳው*



4. ኃጢያት ምን ማለት ነው?

   በሃሳብ ወይም በድርጊት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መተላለፍ ወይም መቃወም ኃጢያት ይባላል በዚህም መሠረት ኃጢያት በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ተገልጿል።

   4.1 ዓላማን ወይም ግብን መሳት። ዘፍ 3÷6
   4.2 በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ወይም አለመታዘዝ። ሮሜ 1÷28-32
   4.3 በጐ እንደሆነ አውቆ አለማድረግ። ዘፍ 4÷7 ያዕ 4÷17
   4.4 በክርስቶስ አለማመን። ዮሐ 16÷8
   4.5 ጥርጥርና ያለእምነት የሆነ ነገር ሁሉ። ሮሜ 14÷23

## II. የእግዚአብሔር ምህረት

*እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ምህረቱን በመግለጥ የተበላሸውን ሕብረት አደሰ /አስተካከለ/*

1. በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ሰው ከእግዚአብሔር ታረቀ። ሮሜ 5÷9
2. ሰው በኢየሱስ በኩል ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ድፍረት ተሰጠው። ኤፌ 2÷18
3. ከእግዚአብሔር ምህረትን ስለተቀበልክ ከእርሱ ጋር ህብረት የማድረግ ብቃት አለህ።

   3.1 ምህረት ምንድን ነው?

      ሀ. በኃጢያት ምክንያት የሚመጣውን ኩነኔና ፍርድ ማስቀረት። ሮሜ 3÷2 ሮሜ 8÷1

      ለ. የማይገባህን ብቃት እንደተገባህ አድርጎ መስጠት። 2ኛ ቆሮ 4÷1
      ሐ. ከኃጢያት ኃይልና ከኃጢያት ውጤት መዳን። ኤፌ 2÷4-5

   3.2 የምህረት አስፈላጊነት

      ሀ. የሰው ልጅ ሁሉ ከኃጢያት ፍርድ በታች ስለሆነ። ሮሜ 2÷23
      ለ. በሰው በራሱ መልካም ነገር ለማድረግ ቢሞክርም እንኳን በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ሆኖ ስለተገኘ። ኢሳ. 64÷6

ሐ. ሰው ያለ እግዚአብሔር ምህረት የዘለዓለም ህይወት ማግኘት ሥለማይችል:: 1ኛ ጢሞ.1÷14-16

3.3 ምህረትን ተቀብለሃል

ሀ. እግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ህይወትን ሰጠህ:: ኤፌ 2÷2-4

ለ. እግዚአብሔር ምህረትን ስለሚወድ ኃጢያትህን ተወልህ:: ሚክ 7÷18-19

## ⅢII. ቅድስና

1. ቅድስና ምንድን ነው?

ሀ. ቅድስና መለየት ነው:: 2ኛ ቆሮ 6÷14-18
ለ. በክርስቶስ ኢየሱስ ባገኘነው ጽድቅ እንድንኖር እግዚአብሔር በእኛ የሚሰራው ከኃጢያት የመለየት ሥራ ነው::
ሐ. ከኃጢያት ኃይል መዳን ነው::

2. የቅድስና አስፈላጊነት

ሀ. መቀደሳችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ:: 1ኛተሰ. 4÷3 እና ኤፌ 5
ለ. ያለ ቅድስና እግዚአብሔርን ማየት ስለማይቻል:: ዕብ 12÷14
ሐ. በምድር የምንኖርበት ዓላማ እርሱ ሥለሆነ:: 2ኛ ቆሮ 6÷17 «ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኩሡንም አትንኩ»

3. የቅድስና አስፈላጊነት

*ለአገልጋዩ:-*

*ምንም እንኳ አማኙ በክርስቶስ ባገኘው ደህንነት የዘለዓለም ህይወት ወራሽነትን ያገኘ ቢሆንም ነገር ግን ይህንን ህብረቱን በየዕለቱ መጠበቅ እንዳለበት የምታሥረዳበት ትምህርት ነው::*

3.1 ንስሃ በመግባት በኢየሱስ ደም ከኃጢያት ነፃ ትሆናለህ:: 1ኛ ዩሐ1÷5-10

ሀ. ስህተት እንደሰራህ ባወቅህ ጊዜ ወዲያው ከእግዚአብሔር ይቅርታን ጠይቅ:: ማቴ 26÷75
ለ. በሰራኸው ሥራ ሰዎችን በድለህ ከሆነ ይቅርታ መጠየቅ ይገባሃል:: ማቴ 5÷24
ሐ. ጥፋትህን አምነህ ይቅርታን ስትጠይቅ እግዚአብሔር ይቅር ሊልህ የታመነ ነው:: 1ኛ ዩሐ 2÷1



መ. የእውነተኛ ንስሃ ባህሪ ምሳ. 28÷13

- ኃጢያት እንደሰሩ ማመን
- ይቅርታ መጠየቅ /መናዘዝ/
- መተው ዳግም አለመሥራት አለማሰብ

3.2 ኃጢያት አለማድረግን በአንተ የሚሰራው እግዚአብሔር ነው:: ፊሊ 2÷12,13

## የምዘና ጥያቄ አምስት

1. የሰውና የእግዚአብሔር ህብረት በሰው ፍጥረት መጀመሪያ ላይ ምን ይመስል ነበር?
2. በሰው ኃጢያት ምክንያት የእግዚአብሔርና የሰው ሕብረት ምን መልክ እንደያዘ አስረዳ
3. ኃጢያት ማለት ምን ማለት ነው?
4. የሰውና የእግዚአብሔር ህብረት እንዴት ታደሰ?
5. ምህረት ማለት ምን ማለት ነው?
6. ቅድስና ምንድን ነው?
7. ቅድስና ለምን ያስፈልጋል?
8. ንስሀ ምንድነው?
9. የእውነተኛ ንስሃ ባህርይ ምን እንደሚመስል አሥረዳ::



ስዕል፡ ፬

## ትምህርት ሰባት

## መንፈስ ቅዱስ

በዚህ ትምህርት ስለመንፈስ ቅዱስ ማንነትና በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚሰራውን አስደናቂ ሥራ እንማራለን:: ኢየሱስ ከመሞቱና ወደላይ ከፍ ከፍ ከማለቱ በፊት ለደቀመዛሙርቶቹ 'ሌላ አፅናኝ እልክላችኋለሁ .... እርሱ ሁሉን የስተምራችኋል ...

እኔ የነገርኳችሁን ያሳስባችኋል ... እኔን ያከብረኛል ጢዜተ... የሚሉና ልብ የሚያንጠለጥሉ ተስፋዎችን ስለ መንፈስ ቅዱስ ተናግሮ ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስም ከመጣ በኋላ ቤተክርስቲያን ታላቁን ተልዕኮዋ በብቃት ለመወጣት ችላለች፡፡ አንዲት ቤተክርስቲያን እንደ ቤተክርስቲያን መንቀሳቀስ የምትችለው በዚህ መንፈስ ቅዱስ መሪነት የምትገዝ የሆነች እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ መሪዋ ያልሆነ ቤተክርስቲያን እንደእቁብ እድር ስብሰባዎች የተለየ ነገር አላት ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም በስብሰባዎቻችን የመንፈስ ቅዱስ መኖር ወይም መገኘት ስብሰባዎቻችን ህይወት ያላቸውና ኢየሱስ የሚከብርባቸው ስለሚያደርጋቸው ነው፡፡

<u>የትምህርቱ ዓላማ</u>

በክርስቶስ ባመነ ሰው ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያድር ለአማኙ ለማስረዳት፡፡

*የቃል ጥናት ጥቅስ*

*መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፡፡ ኤፌ 5÷18*

1. መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

ስለመንፈስ ቅዱስ ማወቃችን፣ እርሱን የበለጠ እንድንጠማው ካገኘነውም በኋላ ደግሞ እንድንጠነቀቅለት ያደርገናል፡፡ ምክንያቱም ይህ መንፈስ የሚያዝን ነውና፡፡

1.1 እግዚአብሔር ነው፡፡ ሐዋ 5÷1-5
1.2 ስብዕና አለው፡

ሀ. ስሜት አለው፡፡ ኤፌ 4÷30
ለ. ፈቃድ አለው፡፡ ሐዋ 13÷2
ሐ. ዕውቀት አለው፡፡ 1ቆሮ 2÷10

2. የመንፈስ ቅዱስ ማደር

1.1 የአማኝ ሰውነት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ ነው፡፡ 1ኛ ቆሮ 3÷16-17
1.2 መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት ውስጥ ለዘላለም ያድራል፡፡ ዮሐ 14÷15-17
1.3 ክርስቶስ በአንተ የሚያድረው በመንፈስ አማካኝነት ነው፡፡ 1ኛ ዮሐ 4÷13



መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት ውስጥ የሚሰራው ሥራ

አማኙን ለእግዚአብሔር ብቻ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ያዕ 4÷5

3.1 ኢየሱስን ያስከብራል፡፡ ዮሐ 16÷14
3.2 ያስተምራል፡፡ ዮሐ 14÷26, ኤፌ 1÷17
3.3 ስፀሎት ያግዛል፡፡ ሮሜ 8÷26
3.4 ስመንፈሳዊ ህይወት ጥንካሬ ይሰጣል፡፡ ኤፌ 3÷16-17
3.5 ያጽናናል፡፡ ዮሐ 14÷26

4. መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ቢኖርም በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት /በቁጥጥር ሥር መሆን/ ያስፈልግሃል፡፡ ኤፌ5÷18

5. ለመንፈስ ቅዱስ ልትሰጠው የሚገባ ምላሽ

ሀ. አታሳዝነው፡፡ ኤፌ 4÷30
ለ. የሚያስተምርህን ተግባራዊ አድርግ፡፡ ዮሐ 16÷13

6. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማቴ 26÷69-75
ሐዋ. 2÷14-40

*ለአገልጋዩ:-*

*በቅድሚያ ከላይ የተጠቀሱትን ምዕራፎች ለየብቻ አስጠናው ቀጥሎም በሁለቱ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሐከል ያለውን ልዩነትና ልዩነቱን ያመጣው ደግሞ ምን እንደሆነ እንዲያስረዳ እድል ስጠው፡፡*

7. ማጠቃለያ

ያለ መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስን ለማክበር መሞከር ውድና አዲስ ሞዴል የሆነችውን መኪና ያለነዳጅ ዘይት ለመንዳት እንደ መሞከር ሊታይ ይችላል፡፡ መንፈስ ቅዱስን መሞላት ጌታ ኢየሱስን አምኖ ለተቀበለ ሰው ሁሉ የተሰጠ መብት ሲሆን በሌላ አነጋገር በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥሩ ሥራ መሆን ማለት ነው፡፡

*ለአገልጋዩ:-*

*ትምህርቱ በአዲሱ አማኝ ውስጥ ተግባራዊ የሆነ ለውጥ እንዲያመጣ እንደተሰጠን ፀጋ መጠን በእምነት አማኙን*

*ለእግዚአብሔር በፀሎት ብታስረክበው ከጌታ ጋር ላለው ጉዞ በብዙ ይረዳሃል።*

## <u>የምዘና ጥያቄ</u>

1. መንፈስ ቅዱስ ማነው?
2. መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ህይወት ውስጥ እንዴት ያድራል?
3. መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት ውስጥ ከሚሠራቸው ሥራዎች አራቱን ጥቀስ።
4. ለመንፈስ ቅዱስ መስጠት ካለብህ ምላሽ ሁለቱን ግለጽ።



ስዕል:፭



## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>በክርስቶስ የማመን ዋስትና</u>

<u>ለአገልጋዩ:</u>

**I. የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ: -**

1. ትምህርቱ በተለይ በምዕራፍ ሁለት ትምህርት አራት ላይ የተዘረዘሩትን አበይት ቁም ነገሮች አካቶ የያዘ ነው።
2. ነገር ግን የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ እነዚህን መሠረታዊ የክርስትና እምነት አዕማድ ትምህርቶች አዲሱ አማኝ በጥልቀት እንዲረዳው ለማሥቻል ነው።
3. ምናልባት በዚህ ምዕራፍ ላይ የተካተቱት ትምህርቶች በምታገለግልበት ቤተክርስቲያን ውስጥ በሌላ የማሥተማር ዘዴና አገልግሎት የተካተቱ ከሆኑና ጊዜ ማባከን መሥሉ ከተሠማህ ሙሉ ለሙሉ አልፈኸው ወደ ቀጣዮቹ ምዕራፎች ልትዘልቅ ትችላለህ።

**II.** ማንም ሰው በሥጋ ከእናቱ ከአባቱ ተወልዶ ወደዚች ምድር ከመጣ በኋላ ነፍስ ሲያውቅ የሚጠይቀው ጥያቄ ለምን ወደዚህች ምድር መጣሁ የሚል ይሆናል። ይልቁንም ዋስትና በሌለው ህይወትና ኑሮ ውስጥ የሚኖር ከሆነ ጥያቄው የሁልጊዜ ጥያቄ ሲሆንበት ይኖራል። እግዚአብሔርም ዳግም በክርስቶስ የመወለዳችንን ወደዚህች ምድርም የመምጣታችንን ምስጢር በቃሉ አስቀምጦልናል።

የዚህን ዓለም ሥርዓት ብንመለከት ሁሉ ነገር በዋሥትና የተጠበቀ እንዲሆን የሰዎች ሁሉ ፍላጎት ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ምሳሌዎች የነገሩን እውነትነት የበለጠ ያረግጡልናል።

ሰዎች ትዳር ከመመስረታቸው በፊት በትዳር ውስጥ ሊያኖራቸው የሚችል በቂ ሃብትና ንብረት እንዲሁም አስተማማኝ ወይም ዋስትና ያለው የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው

ይሻሉ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደዚህ ምድር ከማምጣታቸው በፊት በተለይ በአደጉ አገሮች አስተማማኝ የመኖሪያ ሁኔታ ገና ለሚመጡት ልጆቻቸው ይፈጥራሉ:: አለበለዚያ በእድሉ ይወለድና በእድሉ ያድጋል ተብሎ ዋስትና በሌለው ኑሮ ጠዋት በልቶ ቀን ጦሙን ይውላል:: ማንም ወላጅ ልጁ በዚህ ዓይነት ህይወት እንዲኖር ስለማይፈልግ አስቀድሞ ከመወለዱ በፊት ሰልጁ በቂና አስተማማኝ ሊያኖረው ሊያሳድገው የሚችለውን የኑሮ ሁኔታ ለማዘጋጀት ይጥራል:: ሰዎች ሥራ ከመቀጠራቸው በፊት አሰሪዎቻቸው ከሠራተኞቻቸው ዋስ ሲጠይቁ ሰራተኞቹም ለአሰሪዎቹ የወር ደመወዛቸውን እርግጠኛነት በወረቀት ላይ ተከትቦ እንዲይዙት ያደርጋሉ:: ይህም በቀረው የህይወታቸው ዘመን እንደዋስትና ያገለግላቸዋል:: ከዚህም በተጨማሪ የኢንሹራንስ ድርጅቶች ሰዎች ከእነርሱ የመድህን ዋስትና እንዲገዙ ሁልግዜ ያሳስባሉ:: እንግዲህ ሰዎች ስለዋስትና ይህን ያህል ካሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው የመጨረሻ ህይወት ዋስትና መጠየቃቸው የማይቀር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ በቂና አስተማማኝ የሆነ መልስ ይሰጠናል::

**III.** ሰዎች ወደ ጌታ ከመጡ በኋላ የምናስተምራቸው ትምህርቶች 'እንዲህ መሆን አለብህ' የሚሉ ብቻ ከሆኑ እማኙን 'ከሕግ አርነት' ወጥተሃል እያልነው በተዘዋዋሪ ሌላ ሕግ መጫን ይሆናል:: የእነዚህ ትምህርቶች ዓላማ ለአማኙ በክርስቶስ ብቻ የተደረገለትን በማስተማር፣ ሊሆን ለሚገባው ነገር ብቁ እንደሆነ ለማደፋፈር ነው::



## ትምህርት ስምንት

## እግዚአብሔር ይወድሃል

**የትምህርቱ ዓላማ**

የእግዚአብሔርን ፍቅር ታላቅነት በማስረዳት በዚህ ፍቅር ደግሞ እንዴት መኖር እንደሚቻል ለማስተማር ነው::

**ዋነኛ ጥቅስ** : 1ኛ ዮሐ 4፣10

*" ፍቅርም እንደዚህ ነው:: እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢያታችንም ማስተሠረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም::"*

1. **የፍቅር ዓይነቶች**

ግሪኮች ፍቅርን በቋንቋቸው በተለያየ ዓይነት መልኩ ይገልጹታል:: የመጀመሪያው አጋፔ የሚባለው የፍቅር ዓይነት ሲሆን ይህም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለን የፍቅር አንድነት ያሳያል:: ሁለተኛውን ጾታዊ ፍቅርን ደግሞ ኤሮስ ሲሉት ሶስተኛውን ቤተሰባዊና ጓደኛዊ ፍቅር ፊሊያ በማለት ይጠሩታል:: በዚህ ትምህርት እኛ የምንመለከተው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ይልቁንም እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ድንቅ የሆነ ፍቅርን ወይም አጋፔን ነው::

ለአገልጋዩ :

*ከታች የተዘረዘሩትን ጥቅሶች በማንበብ ምን ዓይነት ፍቅርን እንደሚያሳዩ ጠይቀው :: ዘፍ 24 ፥ 64 :: ዘፍ 27 ፣ 1-17:: ዘፍ 22፣1-12*

2. **እግዚአብሔር የወደደን**

2.1 እንዲሁ ወይም ያለምንም ክፍያ ነው::
ኤፌ 2:5, ዮሐ 3:16
2.2 ሙታን በሆንን ጊዜ ነው:: ኤፌ 2:5

2.3 በባህሪው ፍቅር ስለሆነ ::1ኛ ዮሐ 4:8

3. **የእግዚአብሔር ፍቅር ዓላማ**

እግዚአብሔር የወደደን በእኛ ላይ ካለው አስደናቂ እቅድ የተነሳ ነው:: በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር የፍቅር ዓላማ

3.1 ህይወትእንዲሆንልህ፣ እንዲበዛልህ /እንዲትረፈረፍልህ / :: ዮሐ 10:10
3.2 ሰላም ሊሰጥህ ዮሐ 14:27
3.3 የዘላለምን ህይወት እንድታገኝ ዮሐ 3:16

4. **በዚህ ፍቅር እንድትኖር ታዘሃል::** ዮሐ 15 ፥ 10

4.1 በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ኃይል፣ በፍጹም ሃሳብ እግዚአብሔርን ውደድ::ሉቃ 10÷27፣ ዘዳ 6÷5
4.2 ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ :: ሉቃ 10፣27 ዘሌ 19፣18

5. **በዚህ ፍቅር የመኖር ውጤት ፣**

5.1 ከእዳ ነጻ መሆን:: ሮሜ 13:8
5.2 ሕግን ሁሉ መፈጸም መቻል:: ሮሜ 13:8-10
5.3 ያለፍርሃት መኖር :: 1ኛ ዮሐ 4:18

6. **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት::** 1ኛ ቆሮ 13:1 - 13

6.1 ያለፍቅር ሁሉ ከንቱ ነው:: ቁ. 1-3
6.2 የፍቅር ባህሪይ ቁ. 4-7

6.3 ለዘለዓለም የሚጸና ፍቅር ብቻ ነው ቁ. 8-13

**ለአገልጋዩ:**

***"ከላይ የተጠቀሰውን ምዕራፍ ቢጋራ አጥኑት"***



**የምዝና ጥያቄ ሰብት**

**ለአገልጋዩ:**

***ከዚህ በኋላ ያሉትን ተጣይ ምዕራፎችና ክፍለ ትምህርቶች ሁሉ የምዝና ጥያቄዎችን ሊመልስ ከጥቅስ ጋር መሆን እንዳለበት አስረግጠህ አስረዳው::***

1ኛ: እግዚአብሔር የወደደህ እንዴት ነው ?
2ኛ: እግዚአብሔር ለምን ዓላማ ወደደህ ?
3ኛ: በፍቅር መኖር ማለት ምን ማለት ነው ?
4ኛ: በፍቅር የመኖር ውጤቶችን ጥቀስ:

## ትምህርት ዘጠኝ

## እግዚአብሔር ተቀብሎሀል

– **የትምህርቱ ዓላማ**

ለአማኙ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደእርሱ የመጡትን እንደተቀበላቸውና የተቀበላቸውንም ወደ ውጪ አውጥቶ እንደማይጥል እርግጠኛነት እንዲያውቅና በዚህም ራሱንና ሌሎችን እንዴት መቀበል እንዳለበት ለማስተማር ነው::

- **የቃል ጥናት ጥቅስ : ሮሜ 15፣7**

*"ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደተቀበላችሁ እንዲሁ እርስበርሳችሁ ተቀባበሉ።"*

## ❖ እግዚአብሔር

1. **ማንነትህን ሳያይ ተቀበለህ ቆላ 3:11**

2. **ከጥፋትህ ተጸጽተህ በመመለስህ ተቀብሎሃል።** ሉቃ 15፡ 11-14

3. **ደካማ በነበርክ ጊዜ ተቀበለህ። ማቴ 11:28-30**

   3.1 ለነፍስህ እረፍትን ሊሰጥህ ተቀብሎሃል።
   3.2 ሸክምህን ሊያራግፍልህ ተቀበለህ።

**ስለዚህ**

4. **እግዚአብሔር እንደተቀበለህ ራስህን ተቀበል** ዮሐ 6፡ 37



ሥዕል 6

5. **እግዚአብሔር እንደተቀበለህ ሌሎችን ተቀበል**



5.1 ቤተሰቦችህን ለእግዚአብሔር ክብር ተቀበል ። 1ጢሞ5:8
5.2 በክርስቶስ ያገኘሃቸውን ወንድሞችና እህቶች ለእግዚአብሔር ክብር ተቀበል። ሮሜ15:7
5.3 በክርስቶስ ትምህርት ያሳደጉህን ቤተክርስቲያንህንና በውስጧ ያሉትን አገልጋዬች ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ተቀበል። 1ጢሞ 5:17

**ለአገልጋዩ**

*የምታገለግለው ሰው ምናልባት በህይወቱ ውስጥ በተለያየ ምክንያት የማይቀበላቸው ሰዎች ካሉ እንዴት መቀበል እንደሚችል በምክር ልትረዳው ይገባል። ወይም ደግሞ ራሱን የመቀበል ችግር ካለበት ይህንን እንዲያስወግድ በፀሎትና በምክር እርዳው።*

**የምዘና ጥያቄ ስምንት**

1 እግዚአብሔር እንዴት ተቀበለህ?
2 ራስህን ተቀበል ሲባል ምን ማለት ነው?
3 ሌሎች ሰዎችን የምትቀበለው እንዴት ነው?

# ትምህርት አስር

## እግዚአብሔር በአንተ አንተም

## በእግዚአብሔር ውስጥ አለህ

**የትምህርቱ ዓላማ**

አማኙን በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ እርሱም በእግዚአብሔር ውስጥ የመኖሩን እርግጠኛነት ለማስተማር ነው።

**የቃል ጥናት ጥቅስ** 1ኛ ዮሐ 4፥16

*"እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል። "*

1. **እግዚአብሔር በማን ውስጥ ይኖራል?**

   1.1 ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ብለው በሚታመኑ። 1ዮሐ 4:15
   1.2 በፍቅር በሚኖሩ ሰዎች ውስጥ። 1ዮሐ 4፥16
   1.3 በሚወዱትና ቃሉን በሚጠብቁ ሰዎች ውስጥ። ዮሐ 14:23

2. **እግዚአብሔር በእርሱ እርሱም በእግዚአብሔር ውስጥ የሚኖር ሰው ምልክት።** ዮሐ 15፥5-11

   2.1 ብዙ ፍሬ ያፈራል። ቁ.5
   2.2 የሚጸልየው ጸሎት መልስ ያለው ወይም ጌታ የሚሰማውና የሚመልስለት። ቁ.7
   2.3 እግዚአብሔርን የሚያስከብር ይሆናል። ቁ.8
   2.4 በፍቅር መኖር። ቁ.9
   2.5 እግዚአብሔርን መታዘዝ። ቁ.10



   2.6 ደስተኛነት። ቁ.11

3. **እግዚአብሔር በእኛ የመኖሩ ምስጢርነት ቆላ1:26-27**

   3.1 ከዘላለም ትውልዶችን ጀምሮ ተሰውሮ ነበር።
   3.2 ይህም የባለጠግነት /የሐብት/ ሁሉ ምስጢር ነው።

**የምዘና ጥያቄ ዘወኝ**

1 ራዕይ 3፥20 ላይ ባለው ቃል መሠረት እነዚህን ጥያቄዎች መልስ

- ጌታ ለምን በደጅ ቆመ?
- እንዲገባ ምን መደረግ አለበት ?
- ቢገባ ምን ለውጥ ይመጣል

2. እግዚአብሔር በማን ውስጥ ይኖራል?
3. እግዚአብሔር በእርሱ እርሱም በእግዚአብሔር ውስጥ የሚኖር ሰው ምልክቱ ምንድነው?

# ትምህርት አስራ አንድ

## በእግዚአብሔር ተመርጠሃል

**የትምህርቱ ዓላማ**

አማኙ በእግዚአብሔር በተመረጠበት መጠራት ጸንቶ እንዲኖር ግልጽ አድርጎ በማስረዳትና ለማበረታታት ነው።

**የቃል ጥናት ጥቅስ ኤፌ 1:4**

*"ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን ::"*

እግዚአብሔር በእቅድ ስለሚሰራ እድል ወይም አጋጣሚ አሊያም ግምት በእርሱ ዘንድ ፈጽሞ የለም:: በመዝሙር መጽሐፍ በምዕራፍ 139:16 ላይ ' ያልተሰራ አካሌን አይኖችህ አዩኝ፣ የተፈጠሩ ቀኖች አንድስ እንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ ' እንደሚል እግዚአብሔር እኛን ያወቀን የመረጠን ገና ዓለም ከመፈጠሩ በፊት መሆኑን ለመረዳት እንችላለን::

1. **ምርጫው ከእግዚአብሔር እንጂ ከአንተ አይደለም**

1.1 *መራጩ አንተ አይደለህም:: የመረጠህ ኢየሱስ* ክርስቶስ ራሱ ነው:: ዮሐ 15÷16

2.2 በሰይጣን መንግስት ቁጥጥር ስር የነበረ ሕይወት ስለነበረህ እርሱን ለመምረጥ አቅም አልነበረህም:: ኤፌ 2፤1-3

2. **ለመጠራትህም ሆነ ለመመረጥህ ከአንተ የሆነ ምንም ምክንያት የለም**:: 1ቆሮ 1:27-29

2.1 በዓለም ላይ ከአንተ የተሻለ እውቀት፣ ሃብት፣ ክብርና ዝና ያላቸው ሰዎች እያሉ እግዚአብሔር አንተን መረጠህ

2.2 እግዚአብሔር በዓለም ያለው ብልፅግና ጥበብና ኃይል ምንም እንዳይደለ ሊያሳይና በዚህም ዓለምን ሊያሳፍር አንተን መረጠህ::

2.3 አንተም በምንም ነገር ትምክህት እንዳይኖርህና በእርሱ ብቻ ትመካ ዘንድ መረጠህ::

3. **መጠራትህንና መመረጥህን በመመልከት በትጋት ጽና ::** 2ጴጥ 1:911

3.1 ከትናንት ይልቅ ዛሬ መትጋት ይጠበቅብሃል::
3.2 የቀደመው ኃጢያትህ መንጻቱን አትርሳ::
3.3 ይህንን ሁልጊዜ ብታስታውስ ከቶ አትሰናከልም::



3.4 በዚህም ወደ ክርስቶስ መንግስት መግባት በሙላት ይሰጥሃል::

4. **የመመረጥህ የመጨረሻ ግብ ክብር ነው::** ሮሜ 8:29-30

**የምዘና ጥያቄ አስር**

1. እግዚአብሔር እንዴት መረጠህ ?
2. ለመጠራትህና ለመመረጥህ ከአንተ የሆነ አንዳች ነገር ነበርን? ከሌለ እንዴት?
3. የመጠራትህ የመጨረሻ ግብ ምንድነው?

## ትምህርት አሥራ ሁለት

## ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ተጠርተሃል

**የትምህርቱ ዓላማ**

አማኙ ያለፈ ሕይወቱ በጨለማ እንደነበረ በማስረዳት በአሁኑ ኑሮው እንዲደነቅና በዚህም እግዚአብሔርን እንዲያከብር ለማስተማር::

**የቃል ጥናት ጥቅስ** መዝ 139፤12

*"ጨለማ በአንተ ዘንድ አይጨልምምና ሌሊትም እንደቀን ታበራለችና::" መዝ 139:12*

1. **ቀድሞ በድቅድቅ ጨለማ ነበርክ**

   1.1 በኃጢያት መኖር በጨለማ መኖር ነው:: ዮሐ 5:10
   1.2 ያለክርስቶስ መኖር በጨለማ መኖር ነው:: ዮሐ 12:46
   1.3 ክርስቶስን አለማወቅ በጨለማ መኖር ነው:: ዮሐ 1:9-10
   1.4 ያለተስፋ መኖር በጨለማ መኖር ነው:: 1ተሰ4:13

2. **ክርስቶስ በእርሱ የሚያምኑትን ከጨለማ ሊያድን ብርሃን ሆኖ ወደዚህች ምድር መጣ::** ዮሐ 12:46, ዮሐ 1:15

3. **እንተን እግዚአብሔር ከጨለማው ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራህ የእርሱን በጎነት እንድትናገር ነው::** 1ኛ ጴጥ 2:9

4. **ሰው ብርሃንን የሚጠላው ክፉ የሆነ ሥራውን ስለሚገልጥበት ነው::** ዮሐ3 :18-21

5. **ስለዚህም በቀን እንደምትሆን በአግባብ ተመላለስ::** ሮሜ 13:11-14

**<u>የምዘና ጥያቄ አስራ አንድ</u>**

1. ቀድሞ በጨለማ ነበርህ ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ክርስቶስ የዚህ ዓለም ብርሃን ሆኖ ሲመጣ ሰዎች ያልተቀበሉት ለምንድነው?
3. ሰው ብርሃንን የሚጠላው ለምንድን ነው?
4. በዚህ ትምህርት መሠረት እግዚአብሔር ከጨለማ እንተን የጠራህ ለምን ዓላማ ነው ?





# <u>ትምህርት አሥራ ሶስት</u>

## <u>ኃጢያትህ ተሰርዬልሃል /ተደምስሶልሃል/</u>

**የትምህርቱ ዓላማ**

እግዚአብሔር ኃጢያታችንን በልጁ ሞት ምክንያት እንደተወልን ወይም ይቅር እንዳለን ለማስረዳት ነው::

**የቃል ጥናት ጥቅስ ሮሜ 5፡6**

*" ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢያተኞች ሞቷልና::"*



1. **ጻድቅ የለም አንድ እንኳ ሁሉም ኃጢያትን ሰርተዋል፣ የእግዚአብሔር ክብር ጎድሏቸዋል::** ሮሜ 3:23, ሮሜ 3:11

**2. የዚህ ሁሉ ኃጢያተኛ ደሞዝ ሞት ነበር:: ሮሜ 6:23**

ሞት ስንል ሁለት ዓይነት ነው:: አንደኛው የመንፈስ ሞት ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የመንፈስ ህብረት መቋረጥና የሰይጣን ባሪያ መሆን ሲሆን፣ ሁለተኛው ሞት ብለን የምንጠራው ደግሞ ወደ አፈር መመለስን ነው::

**3. ክርስቶስ ስለኃጢያት ሞተ:: 1ኛ ቆሮ15:3**

**4. በክርስቶስ ሞት ምክንያት ፣**

4.1 ከእግዚአብሔር ቁጣ ድነሃል :: ኤፌ 2:5
4.2 ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀሃል:: 2ኛ ቆሮ 5÷18-19
4.3 ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን አግኝተሃል:: ቆላ 2:13
4.4 የእዳ ጽሕፈትህ ተደምስሷል :: ቆላ 2:13
4.5 ሰይጣን ድል ተነስቷል :: ቆላ 2:15
4.6 ከብረሃል ሮሜ 8:30

**5. የኃጢያትህ መደምሰስ / መዳንህ/**

5.1 የእግዚአብሔር የምህረቱ ባለፀግነት ውጤት ነው:: ኤፌ 2:4
5.2 የፍቅሩን ታላቅነት ያሳያል:: ኤፌ 2:5
5.3 የእግዚአብሔር ስጦታ ነው:: ኤፌ 2:8
5.4 . ከአንተ የሆነና የምትመካበት አንዳች ነገር የለህም :: ኤፌ 2:9
5.5 መልካሙን ሥራ ለመስራት በክርስቶስ እንደገና መፈጠርህን ያሳያል:: ኤፌ 2:10

**የምዘና ጥያቄ**

1. የኃጢያት ደሞዝ ሞት ነው ማለት ምን ማለት ነው?
2. በክርስቶስ ሞት ምክንያት ያገኘሃቸውን አራት ዋና ዋና ነገሮች ጥቀስ :
3. ለኃጢያትህ ይቅርታ ማግኘትህ ከአንተ ሁኔታና ከእግዚአብሔር ባህርይ አንፃር የተረዳኸውን ግለጽ:



# ትምህርት አሥራ አራት

## የዘለዓለም ሕይወት አግኝተሃል

ብዙ ሰዎች ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ይጠይቃሉ:: ይህንን ሕይወት ለማግኘት የራሳቸውን ብርቱ የሆነ ጥረት ሲያደርጉና ራሳቸውን የዘላለም ሕይወት ያስገኝልናል ብለው ላመኑበት ነገር ሲያስገዙ እንመለከታለን:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ለዚህ በቂና አስተማማኝ የሆነ መልስ አለው::

**የትምህርቱ ዓላማ**

ስለዘላለም ሕይወት እርግጠኛነትና ይህም ሕይወት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ብቻ እንዳለ ለማስተማር ነው::

**የቃል ጥናት ጥቅስ**

*"እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው :: ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም:: ዮሐ 5:24 "*

**1.ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ስለሆነ ዘለዓለማዊ ነው::**

እግዚአብሔር ለዘላለም እንደሚኖር እንዲሁም የሰው ልጅ ለዘላለም እንዲኖር ተፈጥሯል:: ልዩነቱ የሰው ልጅ ለፍጥረቱ መጀመሪያ ሲኖረው ለእግዚአብሔር ግን ከ እስከ ብለን ጅማሬውን ለመናገር አለመቻላችን ነው:: ዘፍ 1:26,

ሰው — እግዚአብሔር

ጅማሬው ይታወቃል → ፍፃሜው ዘላለማዊ

ዘላለም ↔ ዘላለም

ለአገልጋዩ :- በዚህ ክፍል፣

1.1 ሰው በክርስቶስ አመነም አላመነም ለዘላለም እንደሚኖር::
1.2 እግዚአብሔር ለሰው መኖሪያ ዓለም ሳይፈጠር እንዳዘጋጀ:: 1ኛ ቆሮ 2÷9
1.3 ገሐነመ እሳት ሰው በራሱ ፈቃድ የሰይጣንን መንገድ /አለመታዘዝና አመጽ/ ሲከተል የሚገባበት እንጂ' ለሰው ልጅ ' ብሎ እግዚአብሔር እንዳላዘጋጀው ለአማኙ አስረግጠህ አስረዳው:: ማቴ 25:31-45

2. **የዘላለም ሕይወት ምን ማለት ነው ?**

2.1 ከፍርድ መዳን :: ሮሜ 8:1, ዮሐ3:17
2.2 ከሁለተኛ ሞት መዳን:: ራዕ 20:14-15
2.3 ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ የነበረችውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ መንግስት መውረስ ::ማቴ 25:34 እና 46

3. **የዘላለም ሕይወት ማግኘት የቻልከው እንዴት ነው?**

3.1 በእግዚአብሔር ልጅ በማመንህ::1ኛ ዮሐ 5÷11-12
3.2 የእግዚአብሔር ፍቅር ለአንተ ስለበዛ:: ዮሐ 3:16

4. **የዘላለምን ሕይወት ማግኘትህን በምን ታውቃለህ?**

4.1 በቃሉ ምስክርነት 1ኛ ዮሐ 5:11-13
4.2 በሰጠህ በመንፈሱ 1ኛ ዮሐ 3:24
4.3 በልብህ ፍርድ 1ኛ ዮሐ 3:18-19

**የምዘና ጥያቄ አስራ ሶስት**

1:የዘላለም ሕይወት ምን ማለት ነው ?
2:ዘላለም ሕይወት ያገኘኸው እንዴት ነው ?
3:ዘላለምን ሕይወት ማግኘትህን በምን ታውቃለህ?



# ትምህርት አስራ አምስት

## የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል

ብዙ ሰዎች በሐብታቸው፣ በእውቀታቸው፣ በዜግነታቸው በትውልድ ሐረጋቸው ...ወዘተ ሲመኩና ሲታበዩ ይታያል:: ዳሩ ግን ይህ ሁሉ አንድ ቀን የሚያልፍ ነገር ነው:: እግዚአብሔር የተቀበለን ማንነታችንን ሳያይ እንደሆነ ከዚህ በፊት በነበረን ትምህርት ለማየት ችለናል::
ከተቀበለን በኋላ ደግሞ በእርግጥ ቢመኩበት የሚያስመካ ፣ ማንነትን እንደሰጠን፣ ያም የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ስልጣንና ክብር እንደሆነ በዚህ ክፍለ ትምህርታችንን እናያለን::

**የትምህርቱ ዓላማ**

የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን ምስጢርና ለዚህም ታላቅ ክብር ያበቃንን አዲሱን ውልደታችንን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር ለማሳየትና ታላቅነቱን ለማስረዳት ነው፡

**የቃል ጥናት ጥቅስ**

*"ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው::" ዮሐ 1:12*

1. **የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ኢየሱስን መቀበልና ማመን ያስፈልጋል** ዮሐ 1÷11-13

2. **የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ስልጣን ነው ክብርም ነው::**

2.1 የእግዚአብሔር ልጅን መልክ መምሰል :: ሮሜ 8:29
2.2 የክርስቶስ ወንድም ተብሎ ለመጠራት መቻል:: ሮሜ 8:29 ዕብ 2:13-17
2.3 ከባርነት አርነት መውጣት:: ገላ 4:1-7
2.4 ለባሪያ /ልጅ ላልሆነ/ የማይነገር ምስጢር ማወቅ::ዮሐ 15:15
2.5 እግዚአብሔርን አባ አባት ብሎመጥራት መ ቻል:: ገላ 4፣6

2.6 ወራሽ መሆን። ሮሜ 8:17, ገላ 4:7

**3.የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ መወለድ ምስጢር ነው። ዮሐ 1:13**

**ለአገልጋዩ :-**

*ምስጢርነቱ ሰው በዚህ አእምሮ ሊረዳው ስለማይችል መሆኑን አስረዳው።*

4. ዘርህ ለዘላለም የሚኖር ነው። 1ኛ ጴጥ 1:23

5. አዲስ ቤተሰብ ተቀላቅለሃል ኤፌ 2:19

ለአገልጋዩ :-

*ቤተሰብ የሚለው ቃል ጠለቅ ያለ ዝምድና የሚያመለክት ቃል መሆኑን አስረዳው*

**<u>የምዘና ጥያቄ አሥራ አራት</u>**

1. የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ምን ያስፈልጋል?
2. የእግዚአብሔር ልጅ በመሆን ካገኘሸው ነገር ጥቂቱን ጥቀስ።
3. የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ የመወለድን ምስጢርነት አስረዳ።
4. ዘርህ ለዘለዓለም የሚኖር ነው። እንዴት?
5. የተቀላቀልከው አዲስ ቤተሰብ ምን አይነት ቤተሰብ ነው?



# <u>ትምህርት አስራ ስድስት</u>

## <u>አዲስ ፍጥረት ሆነሃል</u>

እግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት እንድንሆን ቃሉንና መንፈሱን ላከ /ቲቶ 3:5/ ይህ የሆነው ከእግዚአብሔር ምህረትና ቸርነት የተነሳ ነው። እኛም ቃሉን ባመንን ጊዜ በመንፈሱ አማካኝነት ለአዲስ ልደት በቃን። ይህም አዲስ የሆነው ልደት አዲስ ፍጥረት አደረገን እንጂ በእኛ ሥራ ወይም ልዩ ጥበብ አይደለም። ከሁሉም አስደናቂውና አስደሳች የሆነው ዜና በዚህ ዓለም ሳለን ለሚመጣው ዓለም የዜግነት ማረጋገጫ ማግኘታችን ነው። በዚህ ትምህርት አስደናቂውን የፍጥረታችንን ምስጢር እንማራለን።

**የትምህርቱ ዓላማ**

አሮጌው ሰው እንዴት ወደ አዲሱ ሰውነት እንደተለወጠ፣ የአዲሱን ሰው ፍጥረትና ያፈጣጠር ምስጢር ለአማኙ በመግለጥ አዲሱን ኑሮውንም እንዲለማመደው ለመርዳት ነው።

**የቃል ጥናት ጥቅስ** 2ኛ **ቆሮ** 5÷17

"ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው። አሮጌው ነገር አልፏል። እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል"

1. **አሮጌው ሰውና ባህሪው**

እግዚአብሔር በዘላለማዊ እቅዱ መሠረት ሰውን ከአፈር ፈጥሮት ከመንፈሱ እስትንፋስን ከሰጠው በኋላ በምድር ላይ ገዢ ሆኖ እንዲኖር ስልጣን ሰጥቶት አስቀመጠው። ነገር ግን የሰው ልጅ እግዚአብሔር ካቀደለትና እንዲኖር ካዘጋጀለት ቦታ ፈቀቅ ባለ ጊዜ ያንን አስደናቂ የነበረው ኑሮውንና ፍጥረቱን የሰይጣንን ድምጽ ሰምቶ አበላሸው።
በዚህም ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጥል ሆነ ።

እግዚአብሔርም የፈጠረውን ፍጥረት 'አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ ' /ዘፍ 3:19/ ብሎ ረገመው::

1.1 አሮጌው ሰው በእግዚአብሔር ፊት ክብር የጎደለው ነበር::
1.2 አሮጌው ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ፍጹም የሆነ ድፍረት አልነበረውም::
1.3 አሮጌው ሰው የሚሞትና ወደ አፈር የሚመለስ ነበር::

**ለአገልጋዩ :-**

*"ከዚህ በፊት ለአማኙ ወደአስተማርከው ትምህርት በመሄድ የአዲሱን ሰውና የአሮጌውን ሰው ማንነት በማነፃፀር ግልጽ አድርግለት::"*

2. **የአዲሱ ሰው ፍጥረት ዓላማ ኤፌ 2:10**

ማንም ሰው ወደዚህም ምድር የሚመጣው ከሥጋዊ እናትና አባቱ በስጋ ሲወለድ ነው:: ከዘያ በኋላ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምንና እንደ አዳኙ አድርጎ ሲቀበለው ሁለተኛው ልደቱን ያገኛል::

የመጀመሪያው ማለትም ከእናትና ከአባቱ የተወለደው ሰው 'ፍጥረታዊ ሰው ' ሲባል ሁለተኛው ማለት ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ልደት የተወለደው ደግሞ ' መንፈሳዊ ሰው ' ተብሎ ይታወቃል:: ይህ አዲሱ ማለትም መንፈሳዊው ሰው ደግሞ የተፈጠረበት ዓላማ አለው:: ይኸውም፤

2.1 እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ማድረግ:: ኤፌ 2:10
2.2 ክርስቶስን መመሰል :: 1ኛ ቆሮ 11:1
2.3 ለዘላለማዊው ሕይወት መዘጋጀት:: /1ኛ ጴጥ2:11/

**ለአገልጋዩ :-**

*አዲሱ ሰው ያለንበት ምድር ዘላለማዊ እንዳይደለች አስረዳው::*



3. **ፍጥረታዊ ሰው::** 1ኛ ቆሮ 2፣14

3.1 ዳግመኛ ያልተወለደ ::
3.2 የእግዚአብሔር ነገር ለእርሱ ሞኝነት ስለሆነ አይቀበለውም::

4. **ስለዚህ አሁን የምትኖረው ኑሮ የአዲሱም ሰው ኑሮ ይሁን::** ቆላ 3:2-9

**የምዘና ጥያቄ**

1. አሮጌው ሰው ባህሪው ምን አይነት ነበር?
2. የአዲሱ ሰው የፍጥረቱ ዓላማ ምንድን ነው?
3. የአዲሱ ሰው ኑሮ ምን ዓይነት ነው ?

# ትምህርት አሥራ ሰባት

## በእግዚአብሔር ፊት ብቃትን አግኝተሃል

ሰው ሁልጊዜ ከሌላ ነገር ጋር አወዳድሮ ራሱን ከፍ ወይም ዝቅ ባደረገበት መጠን ልክ ብቃቱን በዚያው ይመዝነዋል:: ማንም ሰው 'በቅቻለሁ' ብሎ የሚያስበው ብዙ ነገር እንዳለው እንዲሁ 'አልበቃም' ብሎ ድምዳሜ ላይ የደረሰበትም ብዙ ነገር በሕይወቱ ይኖረዋል::

ለአንድ ሰከንድ ራሳችንን ከኃያሉና ከብርቱ እግዚአብሔር ጋር አስተያይተን እኛ በእርሱ ፊት ራሳችንን እንደ ትቢያ ብንቆጥር የሚያስደንቅ አይሆንም አስደናቂው ነገር 'በእርሱ ፊት የመቆምን ብቃት አግኝተናል ' ብለን በድፍረት ለመናገር የቻልን ጊዜ ነው:: በዚህ ትምህርት በእግዚአብሔር ፊት የመቆም ብቃትና በሕይወታችን ያመጣውን አስደናቂ ለውጥ እንመለከታለን::

**የትምህርቱ ዓላማ**

አማኙን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ብቃትና ድፍረት ምን ያህል እንደሆነ ለማስረዳት ነው::

**የቃል ጥናት ጥቅስ**

*"በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን:: 2ኛ ቆሮ 3:4"*

1. **እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ላይ ብቃት አለው::** ኢዮ 36:5
   1.1 ኤልሻዳይ ነው ሁሉን ማድረግ ይችላል::
   1.2 ሙሉዕ ነው በሁሉ ስፍራ ይገኛል::
   1.3 ፍጹም ነው በምንም ነገር አይሳሳትም ዘፍ 17፤1-3
2. **ክርስቶስ ስለኃጢያትህ ስለሞተልህ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ በእርሱ በኩል ብቃት አለህ::** 1ኛ ጴጥ 3፤18
3. **እግዚአብሔር አባ አባት ብለህ የመጥራት ብቃት አለህ::** ገላ 4:4-7 ሮሜ 8÷15

ማንም ሰው ላልወለደው ልጅ አባት ሊሆን አይችልም:: ቢባል እንኳ አባት ከሚለው በፊት ሌላ ቅጥያ አስከትሎ ነው:: /የእንጀራ፣ የአይን፣ አሳዳጊ...ወዘተ/ እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አባት ነው:: ከፊት ለፊትም ቅጥያ ቢኖር ፍፁም: ታማኝ: እውነተኛ ... የሚል



ብቻ ነው:: ከእግዚአብሔር የተወለደ ደግሞ እግዚአብሔርን አባ አባት ብሎ ሊጠራ መብቱ ነው:: ብቃትም አለው::

4. **በእግዚአብሔር ፊት የመፀለይ ብቃት አለህ ::** ዮሐ 16:23

በእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የምንለምነውን ሁሉ ሊሰጠን ቃል ገብቶልናል:: በፊቱ ለምነን እንድንሰማ ብቃት የሆነን ደግሞ ክርስቶስ ነው:: ስለዚህ ያለ ምንም ከልካይ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ስም ለመፀለይ ብቃቱ አለህ::

5. **ዓለምን፣ ሰይጣንንና ሥጋን አሸንፈህ ክርስቶስን ለማክበር ብቃቱ አለህ::**
   5.1 ዓለምን ዮሐ 16:33,ቲቶ 2:12-13
   5.2 ሰይጣንን ሉቃ 10:19, ማር 16:17
   5.3 ሥጋን ገላ 5:24
6. **በክርስቶስ ሁሉን የመቻል ብቃቱ አለህ ::** ፊል 4:13

**ለአገልጋዩ**

*ሁሉን መቻል ማለት ከተጠቀሰው ቃል ውጪ ሌላ ትርጉም እንዳይሰጠው*

**የምዘና ጥያቄ አስራ ስድስት**

1. እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ብቃት አለው ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ድፍረት ያገኘነው እንዴት ነው ?
3 በህይወት ለማሸነፍ አስቸጋሪ የሆነብህ ነገር አለ? እስቲ ከሚያገለግልህ ሰው ጋር ተመካከር::

# <u>ምዕራፍ አራት</u>

# <u>ደህንነት</u>

<u>ለአገልጋዩ :</u>

**የትምህርቱ ዓላማ**

*ሰዎች ስለ ደህንነት ያላቸውን አመለካከት በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መልክ ለማስያዝ እና 'ደህንነት ' የሚለውን ቃል ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ሶስት የጊዜ አቅጣጫዎች አንፃር በማሳየት ትምህርቱን የሚከታተለው ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በሚያጠናበት ወቅት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደህንነት በሚናገረው ነገር ግራ እንዳይጋባ ለማገዝ ነው::*





**መነሻ ጥቅስ**

***ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም፣ ቤዛነትን በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው::*** *1ኛ ቆሮ 1:31*

የደህንነት ጥያቄ በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ የሚገኝና ሰው ከውድቀቱ ጀምሮ እንዲመለስለት የሚናፍቀው አብይ ጉዳይ ነው::ጥያቄው ያለምክንያት የመጣ ሳይሆን ሰው ለሕይወቱ ዋስትናና ሰላም ሲሻ ትኩረት የሚሰጥበት ጉዳይ ስለሆን ነው:: ነገር ግን ሰው ቀላል የሆነውን የእግዚአብሔርን የደህንነት መንገድ ከመቀበል ይልቅ የራሱን የደህንነት መንገድ ሊፈጥር ሲሞክር ይታያል::

በእርግጥ እግዚአብሔር ያለእኛ ጣልቃ ገብነት በራሱ ብቻ የሰራውን የደህንነት እቅድ ሳስተዋለ ሰዎች ይህንን እውነት ለመቀበል ቢከብዳቸው አያስደንቀውም::

የምታገለግለው ሰው አሁን ስለመዳኑ በቂ የሆነ ነገር ተረድቷል ብለህ ልታስብ ትችላለህ:: ነገር ግን እርሱ በግሉ መጽሐፍ ቅዱስን በሚያጠናበት ጊዜ ወይም ካላመኑ ሰዎች ጋር በክርስቶስ ስለሚገኝ የዘለዓለም ህይወት ሲነጋገር ግራ የሚያጋባ ነገር ሊገጥመው ይችላል::

በዚህ ክፍለ ትምህርት አማኙን ግራ ሊያጋቡ የሚችሉ አንዳንድ መሠረታዊ የደህንነት ባህርያትን እንማራለን::

እስቲ እነዚህን ምሳሌዎች ልብ በል:: የምታገለግላቸውን ሰዎች ምን ያህል ታውቃቸዋለህ::

*1. ይልማ ወደዚህ ቤተክርስቲያን ከመምጣቱ በፊት ከእናት ከአባቱ በተቀበለው እምነት ወግ አጥባቂ ሐይማኖተኛ ሰው ነበር:: አንድ ቀን አንድ ጓደኛው ለምኖትና ሰውን ተደብቆ እሁድ አምልኮ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ቻለ::*

*የዚያን ቀን ይልማ ሰባኪው "ጌታን የምትቀበሉ ጥሪ አደርጋለሁ " ሲል ተነስቶ ቆመ:: በሁኔታው ይዞት የመጣው ሰው በጣም ተገርሟል::በኋላ ራሱ ይልማ ሲመሰክር ልቡ የተነካው ከቃሉ በፊት ይዘመር በነበረው መዝሙር ነው:: ዛሬ ያን ውሳኔ ከወሰነ ስድስተኛ ወሩ ነው:: ነገር ግን ስለደህንነቱ ሲያስብ ሁልጊዜ ይጨነቃል:: <u>ለደህንነቱ</u> ብዙ ይጸማል፣ ይፀልያል ቤተክርስቲያንም አይቀርም::*

ከእያንዳንዱ ሰው ጋር ያለው ህብረት በጥንቃቄ ነው:: ሁሌ ማታ ማታ ምናልባት በድያቸው ይሆን እያለ መበደሉን ለማያውቀው ኃጢያት እያለቀሰ ንስሃ ይገባል:: ጌታን በጣም ይወዳል:: ከእርሱ ከሚለይ ሁሉን ነገር ቢያጣ ይመርጣል:: ይልማ ለደህንነቱ ያን ያህል መጨነቅ የጀመረው የፊልጵስዮስ መልዕክት ምዕ 2÷12 ላይ ያለውን ቃል ካነበበ ጊዜ ጀምሮ ነው:: "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ"

ነገር ግን ይልማን ያገለግል የነበረው ወንጌላዊ ለብዙ ወራት ይህንን ፍርሃቱን አልተረዳለትም ነበር::

2. ትርሲት ወደ ቤተክርስቲያን መጥታ ህብረት ካደረገች አንድ አመት ከሁለት ወር ሆኗታል:: ነገር ግን ስለጌታ መምጣት ማሰብ አትፈልግም:: ጌታም መጥቶ እንደሚፈርድባት ራሷን አሳምናለች:: ሮሜ 13፣11-14 " ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደኛ ቀርቧልና::" የሚለውን ቃል ካነበበች ጀምሮ ለእርሷ የፍርዷ ቀን እንደሆነ እያሰበች በሀሊናዋ ትወቀሳለች:: ምክንያቱም በቀንና በአግባብ እየተመላለሰች አልነበረምና::

አገልጋይዋ ቆንጂት ግን ይህን የትርሲት ምስጢር አታውቅም ነበር::

3. ካሳ ጌታን ተቀበልሁ የሚለው የዛሬ አስራ አራት አመት ነው:: ብዙ የስውር ኃጢያቶችን የሚለማመድ ሰው በመሆኑ በውስጡ ሰላም የለውም:: ስለደህንነቱ ግን በማንም ፊት እርግጠኛ ሆኖ ይናገራል:: በእርግጥም ስለዚህ ጉዳይ ተጠራጥሮ አያውቅም:: ሁልጊዜ በአእምሮው ኤፌ 2፣5 ላይ ያለውን ቃል እያሰበ ይጽናናል:: " በፀጋ ድኛለሁ "

የካሳ ቤተክርስቲያን መጋቢ ግን ይህንን የካሣን ሥውር የኃጢያት ልምዶች ታሪክ ለብዙ ዓመት አያውቅም ነበር::

አንዳንዴ አንድን ቃል ለጥጦ መተርጎም ከጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ጋር ፍፁም ተቃራኒ መረዳት ሊያመጣ ይችላል::



የምታገለግለው ሰው በእነዚህ ሳምንታት የገላትያ መጽሐፍን ከያዕቆብ መጽሐፍ ጋር እንዲያጠና አድርገው:: የተረዳውን ጠይቀህ ተወያዩባቸው::




በዚህ ክፍል ላይ ደህንነት በተለያዩ ሶስት የጊዜ ሁኔታዎች ውስጥ ምን እንደሚመስል ለማስረዳት ጥረት እናደርጋለን:: ምንም እንኳ እነዚህ የደህንነት ዓይነቶች በአማኙ ሕይወት ውስጥ በተለያየ ጊዜ የሚፈጸሙ ቢሆንም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን አማኙ ጌታን በተቀበለ ጊዜ የሆኑ ነገሮች ናቸው ::

**ልብ በል**

እነዚህ ከላይ የተገለጡት ቃሎች ትርጉም አንዳንዴ ፍጹም ተመሳሳይነት ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን የትምህርቱ መሠረታዊ ዓላማ ከገባህ አንተን ወይም የምታስተምረውን ሰው ይቀለዋል ብለህ በምትረዳው ቋንቋ መጠቀም ትችላለህ።

**አጭር ማብራሪያ**

1. ***ዳግም መወለድ***

አማኙ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በተቀበለበት ጊዜ ወይም ቅጽበት ማለታችን ነው።

2. ***ቅድስና***

አማኙ ጌታ ኢየሱስን ከተቀበለ በኋላ በየዕለቱ የሚኖረውን ከዚህ ዓለም የተለየ ሕይወት ማለታችን ነው።

3. ***ክብር ( ቤዛነት )***

አማኙ ከዚህ ዓለም ህልፈት በኋላ እግዚአብሔር ለልጆቹ ባዘጋጀው መንግስት ውስጥ የሚኖረውን ሕይወት ማለታችን ነው።





# ትምህርት አስራ ስምንት

## ደህንነት የእግዚአብሔር ጥበብ

**ትርጉም:** *ጥበብ ስንል እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የተጠቀመበትን መንገድ ማለታችን ነው።*

**የትምህርቱ ዓላማ:** ለደህንነታችን ከእግዚአብሔር ጥበብ ውጪ አንዳችም የእኛ አስተዋጽኦ እንደሌለ ለማስረዳት

## ክፍል አንድ

1. **የውይይት ጥያቄዎች**

   1.1 በሰው ፍጥረት የእግዚአብሔር ዓላማ ምን ይመስልሃል
   1.2 ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ለደህንነት ሰው ጥበብ ብሎ ከያዛቸው ጥቂቶቹን ተወያዩባቸው።

**ለአገልጋዩ :**

*ምናልባት የምታገለግለው ሰው እስከዛሬ ድረስ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ውጪ የሆነ መረዳት ሊኖረው ስለሚችል ለውይይታችሁ ትልቅ ትኩረት ሰጥተህ አማኙን ለመገምገም ሞክር።*

*"እነዚህን ከላይ ያሉትን ጥያቄዎች ባለፉት ትምህርቶች የተማራቸው ስለሆነ እርሱ እንዲመልሳቸው አድርግ ።"*

2. **በዘመናት መካከል እግዚአብሔር ለሥራው የለያቸው ሰዎችና የደህንነት እቅድ**

   2.1 ኖህ ዘፍ 6:9-32, 7:23
   2.2 አብርሃም ዘፍ 12:1-4
   2.3 አስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ዘፍ 28:12:27, ዘፍ 32:24:60



ለአገልጋዩ ፡

*በዚህ ላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ብዙ ምሳሌዎች እንዳሉ አትዘንጋ።*

3. **የአሮጌው ቃል ኪዳን /የብሉይ ኪዳን/ ሕግ ።**
ዘፀ 20:1, ዘሌ 26:3, ዘሌ 18:5

ለአገልጋዩ ፡

*ጥቅሶቹ ያለ ማብራሪያ የተቀመጡት ከአንተ ብዙ ስለሚጠበቅብህ ነውና መጽሐፍ ቅዱስህን በሚገባ በማጥናት መዘጋጀት ይኖርብሃል።*

4. **የብሉይ ኪዳን መካከለኞች።**

   4.1 የነቢያት አገልግሎት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው፣
   ዘፀ 7:1-2, ዘሁ 12:6
   4.2 የካህናት አገልግሎት ከሰው ወደ እግዚአብሔር።
   ዘፀ19:6, ዘፀ 31:10

5. **የብሉይ ኪዳን መስዋዕት** ። ዘሌ 16:3-5

## ትምህርት ሁለት

1. **ክርስቶስ የሕግ ፍፃሜ**

   1.1 ሕግን ሁሉ ፈፀመ ። ማቴ 5፣17
   1.2 የሕግን ቅጣት ተቀበለ። ገላ 3፣14

2. **ክርስቶስ የአዲሱ ኪዳን መካከለኛ**

   2.1 ክርስቶስ እንደ ነብይ - ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ተናገረ። ዮሐ 8፣ 34
   2.2 ክርስቶስ እንደ ካህን - ከሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ማለደ /አስታረቀ/። ሉቃ 23፣34 ሮሜ 8፣34 ፣ ዕብ 7፣23-28



3. **ክርስቶስ የአዲሱን ኪዳን መስዋዕት።**
ዮሐ 1:29, ዕብ 9:11, 1ጴጥ 1:18

4. **መዳን በሌላ በማንም የለም ።**
ሐዋ 4:2, ዮሐ 3:36, ዮሐ 3:16, ማቴ 1:21

## *ማጠቃለያ*

*በዚህ ትምህርት እግዚአብሔር ለደህንነት እቅዱ "ከሁሉም የተሻለ" ያለውን ጥበብ ለእኛ ገልጦታል። በዚህም ጥበብ የሰው ልጅ የዘመናት የደህንነት ጥያቄ ፈጽሞ ሊመለስ ችሏል። ይህም ጥበብ ለዚህ ዓለም ሞኝነት መስሉ የሚቆጠር ጉዳይ ቢሆንም ለተቀበለው ግን የዘላለም ሕይወት መሠረት ነው።*
*1ኛ ቆሮ 1፣18*

## የምዘና ጥያቄ አስራ ሰባት

1. ከብሉይ ኪዳን መካከለኞች ሁለቱን ጥቀስ
2. ኢየሱስ የሕግ ፍፃሜ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?
3. ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው ?
4. ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መስዋዕት ነው ስንል ምን ማለታችን ነው ?

# <u>ትምህርት አስራ ዘጠኝ</u>

## <u>ዳግመኛ መወለድ</u>

**የትምህርቱ ዓላማ፡**

እማኙን በክርስቶስ ዳግም የመወለድን ምሥጢር ለማስረዳት

**የቃል ጥናት ጥቅስ** ዮሐ 3፥3

*" ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔር መንግሥት ሊያይ አይችልም "*

1. **የመጀመሪያው ውልደት ሰው ከሥጋ እናትና አባቱ የሚወለደው ውልደት ነው።**

*" ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት"*
ዘፍ 1÷28

2. **ይህኛው ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ አይችልም።**

*" አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ"*
ዘፍ 3÷18

*"ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፣ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም"*
1ኛ ቆሮ 15÷50

3. **ሰው በክርስቶስ ሲያምን ዳግመኛ ከእግዚአብሔር ይወለዳል። ዘሩም ለዘለዓለም የሚኖር ይሆናል እንጂ አይጠፋም።** 1ኛ ጴጥ 1፥23-25

4. **ውልደት የመኖር ጅማሬ ነው።**

*ማንም ሰው መኖር የሚጀምረው ከተወለደ በኋላ ነው ሳይወለዱ መኖር እንደማይቻል ሁሉ ከእግዚአብሔር ሳይወለዱ መዳን ወይም የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ አይቻልም።* ዮሐ 1፥13



5. **በኢየሱስ ያመነ ብቻ ዳግም ተወልዷል።** 1ኛ ጴጥ 1፥3

6. **ዳግመኛ የመወለድ ጥቅም**



6.1 ከኩነኔ መዳን ሮሜ 8:1
ኩነኔ ማለት ስለ አንድ ሰው ወንጀለኛነት ወይንም ኃጢያተኛነት የሚከስ የቅድሚያ ንግግር ነው። ነገር ግን በክርስቶስ በማመን ምክንያት ከኩነኔ ድነናል።

*እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል የሚያፀድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኮንንስ ማነው? ሮሜ 8:33*

6.2 *ዳግም በመወለድ አስፈሪ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቁጣ መዳን ይቻላል።* ሮሜ 5:9

7 **ዳግም መወለድ የፀጋና የእውነት ድምር ውጤት ነው።**

*ቃልም ሥጋ ሆነ ፀጋና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ ዮሐ 1:14*

**ፀጋና እውነት**

ፀጋ ማለት ነፃ ስጦታ ወይም ያለዋጋ የሚገኝ ስጦታ ማለት ሲሆን እውነት ማለት ደግሞ ትክክል የሆነ ወይም ጽድቅ የሆነ ነገር ማለት ነው። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ሲያድነን የተጠቀመበት መንገድ ፀጋን ከእውነት አስማምቶ ነው።

8 . *ዳግም መወለድ የቅድስና መንገድ ጅማሬ ነው።*

ቅዱስ ማለት የተለየ ማለት ነው። አንድ ሰው ዳግም ሲወለድ ልክ በዚያው ሰዓት ተቀድሷል ወይም ተለይቷል። ቅድስና ግን ከዚያ በኋላ በየዕለት ህይወቱ የሚኖረው ህይወት ነው።

9. **ያልተወለደ ሊቀደስ አይችልም።** 1ቆሮ 6፡11

*<u>የምዘና ጥያቄ አስራ ስምንት</u>*

- ዮሐ 3 ላይ ያለው የኒቆዲሞስና በጌታ ንግግር ውስጥ ካለው ታሪክ ተነሥተህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ

1. ኒቆዲሞስ ምን ዓይነት ሰው ነበር?
2. ወደ ጌታ የመጣው በምን ዓይነት ጊዜ ነበር ለምን?
3. ስለዳግመኛ መወለድ ለምን ግራ ገባው?
4. ይህ ሰው ጌታ የተናገረው ነገር የገባው ይመስልሃል?
5. ይህ ሰው ከዚያ በኋላ የተለወጠ ይመስልሃል?

በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች አብረህ ተመልከት
ዮሐ 7፣50-53 , ዮሐ 19፣38-42





# <u>ትምህርት ሃያ</u>

## <u>ቅድስና</u>

ከዚህ በፊት ባየነው ክፍል ስለ ዳግም መወለድ ተምረናል። ይህም እግዚአብሔር በልጁ በኩል በፀጋው እንዲያው የሰጠን እንደሆነ አይተናል። በዛሬው የትምህርታችን ክፍል ደግሞ ስለቅድስና ወይንም ደህንነትን በዕለታዊ ኑሮአችን ውስጥ እናያለን።

ባለፈው ትምህርት ዳግም መወለድ የቅድስና መንገድ ጅማሬ ብለን ነበር ይህም ማለት በመወለድ የተጀመረው የክርስትና ህይወት ኑሮ እስከ ክርስቶስ መምጫ ወይም እኛ ወደ ክርስቶስ እስክንሄድ ሳናቋርጥ የምንኖረው የኑሮ ሥርዓት ነው።

**የትምህርቱ ዓላማ**

አማኙን በዕለታዊ ኑሮው በእግዚአብሔር ፀጋ እርዳታ እግዚአብሔርን በመፍራትና በመታዘዝ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንዴት መኖር እንደሚገባው ለማስተማር ነው።

**የቃል ጥናት ጥቅት** ፡1ኛ ጢሞ 3፣14-16

*"... በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ።"*

1. **ቅድስና ከአሮጌው አስተሳሰብ ሙሉ ለሙሉ መላቀቅ ነው።**
   ሮሜ 6፡1, ቆላ 3፡8-11

   1.1 ስለእግዚአብሔር ያለን አስተሳሰብና እውቀት ፣
   1.2 ስለ ሰው ያለን አስተሳሰብ ፣
   1.3 ስለራሳችን ያለን አስተሳሰብና አመለካከት፣

2. **ቅድስና ከኃጢያት ኃይል ነፃ መውጣት ነው።**
   ሮሜ 6፡1-2 ለኃጢያት መሞት ነው

3. **ቅድስና በዕለታዊ ኑሮ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ መመላለስ ነው::** 1ኛ ተሰ 4:1-8

4. **ቅድስና እያንዳንዱ የገዛ ሰውነቱን በክብር መያዝ ነው::** 1ኛ ተሰ 4+ 4-5

5. **ቅድስና ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት መራቅ ነው::** 1ኛ ጴጥ 2:11

6. **ቅድስና በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ፤**

   6.1 በቃልና በሥራ ብርቱ መሆን:: ሉቃ 24÷19
   6.2 በንፁህ ህሊና መመላለስ ፤ ሐዋ 24÷16
   6.3 ያለ ነቀፋ መሆን መቻል ፤ 1ኛ ጴጥ 2÷12

7. **ቅድስና የድልና የአሸናፊነት ኑሮ ነው::** ሮሜ 8:37

8. **ቅድስና ለክርስቶስ ቀን መዘጋጀት ነው ::** ኤፌ 4:21-33 , 1ኛ ጴጥ 1÷13

**<u>የምዘና ጥያቄ አስራ ዘጠኝ</u>**

1. በዚህ ክፍል መሠረት ቅድስና ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. ለመቀደስ ከእኛና ከእግዚአብሔር የሚጠበቀው ምንድነው?
3. ቅድስና ለክርስቶስ ቀን መዘጋጀት ነው ስንል ምን ማለታችን ነው ?
4. ለእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያለነቀፋ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው ?





# <u>ትምህርት ሃያ አንድ</u>

## <u>ክብር /ቤዛነት/</u>

ቤዛነት የሚለው ቃል አንድን ባለእዳ ከእዳው ነፃ ማውጣት ወይም ዋጋውን በመክፈል የራስ ማድረግ የሚል ፍቺ ሲሰጥ በ 1981 የመጽሐፍ ቅዱስ እትም ቤዛነትን ደህንነት ይለዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ቤዛነታችን እንደቀረበና በእርሱም እርስ በእርሳችን እንድንጽናና ያስተምረናል:: ሉቃ 21:28, 1ኛተሰ 4:18 :: ይህም ለአንድ አማኝ ትልቁ ክብር ነው::

**የትምህርቱ ዓላማ**

አንድ ክርስቲያን በሕይወት ዘመኑ በሚደርስበት ችግር ወይም በክርስትናው ምክንያት በሚያገኘው ስደትና መከራ የተነሳ ከእግዚአብሔር ሳይርቅና ተስፋ ሳይቆርጥ የተዘጋጀለትን ተስፋ በመመልከት እንዲጽናና እና እንዲበረታታ ለማድረግ ነው::



**የቃል ጥናት ጥቅስ:** ሉቃ 21፤28

*" ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቧልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ :: "*

ይህ ታላቅ ክብር ነው:: አሁን ገና አልተገለጠም:: ምን እንደምንሆንም ሙሉ ለሙሉ ልንናገር አንችልም:: ግን ልንሆን በእግዚአብሔር ከታሰበልን ጥቂቱን ብቻ እንማራለን:: አሁን ምናልባት ይህንን ትምህርት የሚማረው ሰው ወይም ራሱ አገልጋዩ በክርስቶስ በማመን ምክንያት በሚመጣ መከራ ውስጥ ይሆን ይሆናል:: ነገር ግን ገና የቀረ ተስፋ እንዳለህ ባሳየህ ጊዜ ፈጽመህ እንደምትጽናና ጥርጥር የለውም::

1. **የደህንነታችን የመጨረሻ ግብ ክብር ነው:: ሮሜ 8:30**

   1.1 የክርስቶስ ክብር ተካፋዮች ነን:: ሮሜ 8:17
   1.2 የተዋረደው አካል ክቡር አካል ይለብሳል:: ፊል 3:21
   1.3 የሚበሰብሰው /አካል/ የማይበሰብሰውን / አካል/ ይለብሳል:: 1ኛ ቆሮ 15:44
   1.4 ፍጥረታዊው አካል መንፈሳዊውን አካል ይለብሳል:: 1ኛ ቆሮ 15:44
   1.5 የሚሞተው ሥጋ /ሰውነት/ የማይሞተውን ሥጋ /ሰውነት/ ይለብሳል:: 1ኛ ቆሮ 15:53

2. **አሁን በዓለም ላይ ካለው ችግርና መከራ ሙሉ ለሙሉ ነፃ መውጣት::**

   *በዚህ ምድር ላይ የምኖረው ኑሮ ሁልጊዜ በፈተና የተሞላ ቢሆንም እግዚአብሔር ለእኛ ለልጆቹ ዘወትር ከሚሰጠን ፀጋ የተነሳ ከተፅኖዎች በላይ ለመሆን ችለናል:: ፍጹም የሆነና ከውጊያ ውጪ የሆነ እረፍት ግን አይደለም:: በምትመጣዋ የእግዚአብሔር መንግስት ፍጹም ደህንነታችንን ስናገኝ፣*

   2.1 ሐዘን የለም፣ ለቅሶ የለም፣ ጩኸትና ስቃይም የለም:: ራዕ 21:3- 4
   2.2 ሞት የለም:: 1ኛ ቆሮ 15:54-55
   2.3 መርገም የለም:: ራዕ 22:3
   2.4 ጨለማ የለም:: ራዕ 22:5



3.ሁሉ አዲስ ይሆናል

   3.1 አዲስ የዓለም ሥርዓት:: ራዕ 21÷5
   3.2 አዲስ ሰማይ አዲስ ምድር:: ራዕ 21:1
   3.3 አዲስ የአምልኮ ሥርዓት:: ራዕ 21÷22
   3.4 አዲስ የኑሮ ሥርዓት :: ራዕ 21÷23
   3.5 አዲስ ህዝብ :: ራዕ 21÷23

4 **የዘላለም ሕይወትና የዘላለም ሞት ፍርድ::**
ማቴ 25:31-46, ራዕ 20:14-15

5 **ድል የነሱ ይነግሳሉ::**
ራዕ 3:21, ራዕ 22:5

**የምዘና ጥያቄ ሂደ**

1. የደህንነታችን የመጨረሻ ግብ ክብር ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. አሁን ያለን አካል በሚመጣው ጊዜ ምን እንደሚመስል አወዳድረህ አስረዳ ::
3. በምትመጣው መንግስት ያለው አዳዲስ ነገር ምን እንደሚመስል አስረዳ::
4. ስለዘለዓለም ሕይወትና ሞት ፍርድ ያለህን ሀሣብ ግለጥ::
5. ድል የነሱ ይነግሣሉ ማለት ምን ማለት ነው ?

# ምዕራፍ አምስት

# የእግዚአብሔር ባሕርይ

ለአገልጋዩ:-

በዚህ ትምህርት ለአማኙ ከእግዚአብሔር ባሕርያት መካከል የተወሠኑትን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር የምታሥተምርበት ክፍል ነው።

ትምህርቱ አሥፈላጊ የሆነበት ምክንያት አማኙ ሥለ እግዚአብሔር ባሕርይ ጠለቅ ያለ ዕውቀት እንደሚያሥፈልገው አውቆ መጽሐፍ ቅዱስን ጊዜ ወስዶ እንዲያጠናው መንደርደሪያ የሚሆን አሳብ ለመስጠት ነው።

ምዕራፉ ሥር የሰደደ የሥነ መለኮት ትምህርት ለመሥጠት የተዘጋጀ አይደለም። ያንን ማድረግ የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማም አይደለም። ነገር ግን በዚህ ክፍለ ትምህርት የምታገለግለው ሰው የእግዚአብሔርን ባሕርይ ከተለያየ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲያጠና ሥለ እግዚአብሔር ያለው መረዳትና እውቀት ሚዛናዊ እንዲሆን ይረዳዋል።

ይህ ብቻ ሳይሆን የምታገለግለው ሰው የተለያየ ጥያቄዎችን ሊጠይቅህ ስለሚችልና ትምህርቱም ያለህን እውቀት፣ ግንዛቤና መረዳት የበለጠ እንዲሆን ግድ ስለሚልህ ለምታገለግለው ሰው ብቻ ሳይሆን ለአንተም ትልቅ ጥቅም ይሠጥሃል።

እግዚአብሔር ታላቅ ነው
እኛም አናውቀውም። ኢዮ36÷26

*በየጊዜው ከመታወቅ የሚያልፈውን እግዚአብሔርን በሠጠህ ቋንቋ መግለጥና ማሥረዳት እንድትችል በትህትና በጌታ ፊት መሆን እንዳለብህ አትዘንጋ።*



## የእግዚአብሔር ባሕርይ

**የትምህርቱ ዓላማ:**

የእግዚአብሔርን ልዩ የሆነ ባህርያት በማሥተማር፣ አማኙ የሚያመልከውን አምላክ በጥልቀት፣ እንዲያውቀውና እንዲገነዘበው ለመርዳት ነው።

**ዋነኛ ጥቅስ:** ዳን11÷32

*«አምላካቸውን የሚያውቁ ህዝብ ይበረታሉ፣ ያደርጋሉም»*

# ትምህርት ሃያ ሁለት

# እግዚአብሔር ስብዕና /Personality/ ያለው አምላክ ነው

1. እግዚአብሔር አዋቂ ነው /እውቀት አለው/ መዝ 139÷1-16/

   1.1 ያስፈውን ሁሉ ያውቃል:- ቁጥ. 15-16
   1.2 አሁን ያለውን ሁሉ ያውቃል:- ቁጥ. 4
   1.3 ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ ያውቃል ቁ. 2-3
   1.4 በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል፡ ቁ.2፡ ቁ.6
   1.5 ሙሉዕ ነው። ስለዚህ በየትም ቦታ ያለውን ያውቃል። ከቁ.7-11 /በአንድ ጊዜ በሁሉ ሥፍራ መገኘት የሚችል ስለሆነ ሁሉን ያውቃል/

*ለአገልጋዩ:-*

*መዝ. 139÷1-16 የዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ የጥናት ክፍል ስለሆነ በሚገባ አጥንቶ እንዲመጣ አድርገህ ተወያዩባቸው።*

2. እግዚአብሔር ፈቃድ አለው። ዘፍ.2÷16-17

   2.1 እግዚአብሔር ይሁን ይላል /ይፈቅዳል/። ቁ.16
   2.2 እግዚአብሔር እንቢ ይላል /ይከለክላል/ ቁ.17

3. እግዚአብሔር ስሜት አለው።

   3.1 እግዚአብሔር ያዝናል። ኢሳ. 59÷15
   3.2 እግዚአብሔር ይደሠታል። ሉቃ3÷22። ማቴ. 17÷5
   3.3 እግዚአብሔር ይቀናል። ዘፀ 20÷2-5። ዘዳ 4÷24
   3.4 እግዚአብሔር ይጠላል፣ ይወዳል። ሚል.1÷2-3
   3.5 እግዚአብሔር ይገረማል። ኢሳ.59÷16

*ለአገልጋዩ፦*

*እግዚአብሔር ስሜት አለው ብንልም ግብታዊ ስሜት እንደሌለው አስረዳው።*

## ትምህርት ሃያ ሦስት

## እግዚአብሔር ከሁሉ የሚለይ አምላክ ነው

እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ ኢሳ. 40÷18

1. ታላቅ ነው፣ ከመታወቅ ያልፋል፣ ሁሉን ይመረምራል እንጂ በማንም አይመረመርም። ኢዮ 36÷26። ኢዮ 37÷23
2. ዘለዓለማዊ ነው። ጅማሬ የለውም ፍፃሜም የለውም። ኢሳ 40÷28። ራዕ 21÷5። ራዕ. 4÷9-10
3. ፈጣሪ ነው፣ ሁሉ የተገኘ በእርሱ ነው። መዝ102÷25። 2ኛ ዜና2÷12 ዕብ 1÷10-12
4. ብርቱና ኃያል ነው፣ ተወዳዳሪ የለውም። መዝ 150÷2። ኢዮ 36÷5 ኢሳ 40÷25



5. ቅዱስ ነው። ኢሳ 6÷3። ኢሳ 40÷25
6. ሁሉን ቻይ ነው /ኤልሻዳይ ነው/። ዘፍ 17÷1
7. አይፀፀትም። 1ኛ ሳሙ. 15÷29

*ለአገልጋዩ፦*

*በዚህ ሳምንት ከላይ በተማረው ትምህርት መሠረት አንተ ከሠጠኸው ጥቅስ ሌሎች ተስማሚ ጥቅሶችን /ከቁ.1 እስከ 7 ለተዘረዘሩት/ በጽሁፍ አዘጋጅቶ እንዲመጣ አድርግ።*

## ትምህርት ሃያ አራት

## እግዚአብሔር ሊፈራ የሚገባው አምላክ ነው

«እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ህይወት ይመራል» ምሳ 19÷23

1. እግዚአብሔር ተዋጊ ነው። ዘፀ14÷14። ዘፀ15÷3። ኢሳ42÷13
2. እግዚአብሔር ይቆጣል። ቁ.15
3. እግዚአብሔር ይበቀላል። ቁ.14
4. እግዚአብሔር ይቀጣል። ቁ. 12-14

   (2–4:) 2ኛ ነገ. 21-10-15
5. እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ አምላክ ነው። 1ኛ ጴጥ. 2÷23

*ለአገልጋዩ፦*

*2ኛ ነገ. 32÷1-23*

*በዚህ ክፍል ላይ በመነሳት ስለእግዚአብሔር ፃድቅ ፈራጅነት አማኙ ጠለቅ ያለ ጥናት እንዲያጠናና ያጠናውን እንዲያስረዳ አድርግ።*

### የውይይት ጥያቄ

5.1 የሕዝቅያስ መንፈሳዊ ሕይወት ምን ይመስል ነበር?

5.2 ሕዝቅያስ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥታት የሚለይበት ታሪክ ምንድነው?
5.3 ሰናክሬም - ከጦርነቱ በኋላ ያለው ታሪክ ምን ይመስል ነበር?
5.4 በዚህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ፃድቅ ፈራጅነት ያገኘሽውን አዲስ ነገር ግለፅ።

ተጨማሪ ጥቅሶች:- 2ኛ ነገ 25 ÷1-26። ዳን.4÷28-33። ዳን.5÷1-32 ዕብ:12÷5-11። ዕብ12÷25-29። 2ኛ ነገ 14÷15

*ለአገልጋዩ:-*

*እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ባህርያት በአማኞችና በማያምኑ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ አሥረዳው። ነገር ግን ለአማኙ ያለምንም ማመቻመቹ ትክክለኛ የእግዚአብሔርን ባህርይ ማሥረዳት እንዳለብህ አትዘንጋ።*

## <u>ትምህርት ሃያ አምስት</u>

## <u>እግዚአብሔር ሰውን ይወዳል ይጠብቃል</u>

1. ይቅር ባይ መሐሪ ነው። 1ኛ ዜና 21÷15
2. ትዕግሥተኛና ለቁጣ የዘገየ ነው። ዘፀ 34÷6
3. ታማኝ ነው። ዘፀ 16÷34። መዝ 71÷9-18
4. እውነተኛና ጻድቅ ነው።
5. አይለወጥም። ሚል 3÷6
6. እግዚአብሔር ፍቅር ነው። 1ኛ ዮሐ4÷7-10
7. እግዚአብሔር አሥተማሪ ነው። ኢዮ38÷21። ዮና4÷6-7
   ሰውን ወደ ስህተት እንዳይገባ ቀድሞ ያስተምራል ይመክራል።
8. እግዚአብሔር እረኛ ነው ይጠብቃል። ኢሳ40÷11
9. እግዚአብሔር መልካም ነው በመከራም ቀን መሸሸጊያ ነው። ናሆ1÷7

ለአገልጋዩ:-

*ኤፌ 3÷18-19*
*ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ምን ያወራል ተወያዩባቸው።*



# <u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## <u>ቤተክርስቲያንና ስርዓቶቿ</u>

**ለአገልጋዩ :**

*በዚህኛው ምዕራፍ በተለይ ቤተክርስቲያን በዚህም ምድር ላይ የእግዚአብሔርን መንግስት ሥራ በምትሰራበት ወቅት የምታከናውናቸውን ዋና ዋና ሥርዓቶች እናያለን። እነዚህ ሥርዓቶች ደግሞ ተራ ሐይማኖታዊ ሥርዓቶች ሳይሆኑ በጌታ ቃል ትእዛዝ የሚከናወኑ ስለሆነ ዋጋቸው ቀላል አይደለም። ማንኛውም ከጌታ አፍ የወጣ ትእዛዝ ሁሉ ከእርሱ አፍ በመውጣቱ ብቻ ልንታዘዘው ወይንም አሜን ልንለው ይገባል።*

*አንዳንድ ጊዜ ለእኛ አእምሮ እንቆቅልሽ ቢሆንብን ወይንም ባንረዳው እንኳ እግዚአብሔር በሥራው ሁሉ ጻድቅና ትክክል እንደሆነ ግን ለአፍታም ልንዘነጋው አይገባም።*

**የትምህርቱ ዓላማ**

*"አማኙ ቤተክርስቲያን በዚህ ምድር ስለምትፈጽማቸው መንፈሳዊ ሥርዓቶች ከሐይማኖተኝነት ወይም ከልማድ በመነሳት ሥርዓቶችን ከመፈጸም ይልቅ በእውቀትና በመረዳት ወደሚሆን የአምልኮ ሥርዓት እንዲዘልቅ ለመርዳት ነው።"*

በዚህ ትምህርት ሰዎች የአምልኮት መልክ ብቻ ሳይሆን ኃይሉንም እንዲያውቁና እንዲለማመዱ ልታደፋፍራቸው ይገባል።

**"...የአምልኮት መልክ አላቸው። ኃይሉን ግን ክደዋል። ከእነዚህ ደግሞ ራቅ ።"** 2ጢሞ 3፣5

# ትምህርት ሃያ ስድስት

## ቤተክርስቲያን /የአማኞች ህብረት /

**የትምህርቱ ዓላማ፡**

አማኙ የቤተክርስቲያንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማንነትና የህብረትን ጥቅም እንዲገነዘብና ከክርስቲያኖች ሁሉ ጋር በምን ዓይነት ሁኔታ ህብረት ማድረግ እንዳለበት ለማስረዳት ነው።

**የቃል ጥናት ጥቅስ** ፡ 1ኛ ዮሐ 1፣ 3- 4

*" ህብረታችን ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።"*

**1 የቤተክርስቲያን ትርጉም**

ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን እግዚአብሔርን ለማምለክ በአንድነት የተሰበሰቡ የአማኞች ህብረት ነው።

**2 የቤተክርስቲያን ዓይነት**

2.1 ዓለም አቀፋዊ ቤተክርስቲያን

ይህች ቤተክርስቲያን በዓለም ያሉ አማኞች ሁሉ የታቀፉባት የክርስቶስ ኢየሱስ አካል ናት ። *ራዕ* 7:9-10

2.2 አጥቢያ ቤተክርስቲያን

ይህች ቤተክርስቲያን የዓለም አቀፏ ቤተክርስቲያን አካል ስትሆን በአንድ አካባቢ ያሉ አማኞች ህብረት የሚያደርጉባት ቤተክርስቲያን ነች። 1ቆሮ 1:2





**3 የህብረት /የቤተክርስቲያን / ጥቅም**

3.1 ለፍቅርና ለመልካም ሥራ ለመነቃቃት። ዕብ 10:24
3.2 በረከትና ሕይወትን ለመካፈል። መዝ 133፣ 1-3
3.3 እርስ በእርስ በተሰጠን ፀጋ ለመተናነጽ። 1ቆሮ 12:12-13

**4. በህብረት /በቤተክርስቲያን/ ውስጥ ስንኖር ሊኖረን የሚገባ ህይወት ፣**

4.1 ከራሳችን ይልቅ የሌላውን ጥቅም ማሰብ። ፊሊ 2:3-4
4.2 እርስ በእርስ መፋቀር። ኤፌ 4:2-3
4.3 እርስ በእርስ መቀባበል ። ሮሜ 15:7
4.4 መንፈሳዊ መሪዎችን መታዘዝ። ዕብ 13:17
4.5 እርስ በእርስ ሸክምን መሸካከም። ገላ 6:1-2
4.6 የቤተክርስቲያንን አገልግሎት መደገፍ።

- በፀሎት ቆላ 4:2
- በገንዘብ 2ቆሮ 8:2-4
- በሙያ
- በጉልበት
- በእውቀት

5. **ከማን ጋር ህብረት እናድርግ**

5.1 በንጹህ ልብ ጌታን ከሚያመልኩ ጋር። 2ጢሞ 2:22
5.2 በኃጢያት አካሄድ ከማይሄዱ ጋር። 1ቆሮ 15:33

**የምዘና ጥያቄ ሃያ አንድ፡**

1. ቤተክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው ?
2. ቤተክርስቲያን በስንት ይከፈላል ? ግለፀው ?
3. ከክርስቲያኖች ጋር ህብረት ማድረግ አለብህ? ለምን?
4. ከሌሎች /በቤተክርስቲያን/ ያለህ ህብረት መልካም እንዲሆን ምን ማድረግ አለብህ ?
5. ሕብረት ማድረግ የሌለብህ ከምን አይነት ሰዎች ጋር ነው?
6. በዚህ ትምህርት ውስጥ ያጠናኸውን የቃል ጥናት ጥቅስ ፃፍ።





# ትምህርት ሃያ ሰባት

## አምልኮ

**የትምህርቱ ዓላማ**

አማኙ የአምልኮን ምንነት እንዲረዳ ፣ ወደ እውነተኛ አምልኮ እንዲዘልቅና ህይወቱ ሊሆን የሚገባውን ይህን መንፈሳዊ ልምምድ እንዲጀምር ብሉም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምሮን እንዲገነዘብ ለማድረግ ነው።

**የቃል ጥናት ጥቅስ ፡ ዘፀ 20፥3**

*" ከእኔ በቀር ሌሎች አማልእክት አይሁኑሩህ። "*

1. **የአምልኮ ትርጉም**

1.1 እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት እግዚአብሔርን የበላይ በማድረግና ህይወትን በመስጠት መገዛት ማለት ነው።
1.2 ለእግዚአብሔር እንደሚገባው መጠን የሚገባውን መስጠት ማለት ነው። መዝ 18÷3

2. **የአምልኮ አስፈላጊነት**

2.1 እግዚአብሔር መመለክ ስለሚገባው። ራዕ 5:12
2.2 ለማምለክ ስለተጠራን። ዘፀ 5÷1
2.3 ለማምለክ ስለተፈጠርን። ኢዮ 33÷4።ኢዮ 34÷14-15
2.4 ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ለመግለጽ ዮሐ 14:23
2.5 የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል ዘፀ 23:25

3. **እንዴት እናምልክ** ዮሐ 4:24

3.1 በእውነት፡ ለእግዚአብሔር ከልብ በመገዛት።

3.2 በመንፈስ ቅዱስ።

## 4. አምልኮ የሚገለጥባቸው መንገዶች

4.1 በዝማሬ በዜማ ታላቅነቱን በማግለጥ። ኤፌ 5:19
4.2 በመታዘዝ ።1ኛ ሳሙ 15:22
4.3 ችግረኞች በመርዳት ። ያዕ 1:27
4.4 በጾምና በፀሎት። ሐዋ 13:2-3
4.5 በጉባኤ በአንድነት በመሰብሰብ ። መዝ 26÷12
4.6 በመልካም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ወ.ዘ.ተ

**ለአገልጋዩ:**

*እዚህ ላይ ከተጠቀሱት ውጪ አምልኮ የሚገለጽባቸው መንገዶች ብዙ መሆናቸውን አትዘንጋ።*

## 5. አምልኮን ሕይወታችንና ኑሮአችን ማድረግ።

5.1 የምናደርገውን ለእግዚአብሔር ክብር በማድረግ።1ቆሮ 10:31
5.2 ባለን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን በማክበር። ምሳ 3:9
5.3 በህይወት ዘመናችን ሁሉ ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር በመገዛት። መዝ 27÷4

**የምዘና ጥያቄ ሃያ ሁለት**

1. አምልኮ ማለት ምን ማለት ነው ?
2. የአምልኮ አስፈላጊነትን አስረዳ
3. የምናመልከው እንዴት ነው
4. አምልኮ ከሚገለጥባቸው መንገዶች አራቱን ግለጽ።



# ትምህርት ሃያ ስምንት

## ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከር

**የትምህርቱ ዓላማ**

አማኙ ስለምስክርነት አስፈላጊነት በማሳወቅ እንዴት መመስከር እንዳለበትና ውጤታማ ምስክርነትን ገፅታ በማሳየት አማኙን ወደዚህ መንፈሳዊ አገልግሎት ለማነቃቃት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

**የቃል ጥናት ጥቅስ** ሐዋ:1፣8

*"መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ሁሉ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ። "*

## 1. ለምን እንመሰክራለን

1.1 ስለ እግዚአብሔር በጎነት እንድንናገር ስለተጠራን። 1ኛ ጴጥ 2:9
1.2 ትዕዛዝ ስለሆነ። ማር 16:15
1.3 የሰው ልጆች ከዘላለም ሞት እንዲድኑ። ሮሜ 10:14-17

## 2 .እንዴት እንመሰክራለን

2.1 በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪት። ሐዋ 1:8 ሐዋ 16:6-10
2.2 ኢየሱስ በህይወታችን ያደረገልንን በመናገር። ማር 5:19
2.3 እውነትን በፍቅር በመናገር ። ኤፌ 4÷15
2.4 በድፍረት በመናገር ማቴ 10:32

### 3. ውጤታማ ምስክርነት

3.1 መንፈስና ኃይልን በመግለጥ። 1ኛ ተሰ 1÷5። 1ኛ ቆሮ 2÷4
3.2 መልካም የህይወት አኗኗር። ማቴ 5:16
3.3 ውጤትን ለእግዚአብሔር መተው።
 2ቆሮ 2:15-16
3.4. ከማያምኑ ጋር በክፉ ሥራ አለመተባበር።
 ኤፌ 5:11

**ለአገልጋዩ:**

*ምስክርነቱን ከሚያበላሽ ማናቸውም ነገር ራሱን እንዲጠብቅ አስረግጠህ አስረዳው።*

**የምዘና ጥያቄ ሃያ ሶስት**

1. ለሌሎች ሰዎች የምንመሰክርበት ምክንያቱ ምንድነው ?
2. የምንመሰክረው እንዴት ነው ?
3. ውጤታማ ምስክርነት መመስከር የምንችለው እንዴት ነው ?





# ትምህርት ሃያ ዘጠኝ

## ጥምቀት



**የትምህርቱ ዓላማ**

እጩን የውሃ
ጥምቀትን ለመፈጸም
ወደውሳኔ እንዲያደርሰው
ታስቦ የተዘጋጀ ትምህርት
ሲሆን የዚህ ትምህርት
ዋና ትኩረት እጩን ስለ
ውሃ ጥምቀት ምንነትና ጥቅም
በግልጽ ማስረዳት ነው።



**የቃል ጥናት ጥቅስ፡ ማቴ 28፣19**

*"አህዛብን ሁሉ በአብ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃ ችኋቸው ያዘዝኳችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው።"*

### 1. ትርጉም

በአንድ ነገር ሙሉ ለሙሉ መሸፈን ወይንም ከተጽዕኖ በታች መሆን ሲሆን በዚህ ትምህርት መሠረት ጥምቀት ማለት በውሃ መሸፈን ማለት ነው።

### 2. ሌሎች የጥምቀት ዓይነቶች

2.1 የመከራ ጥምቀት
 ሉቃ 12:50
2.2 የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሐዋ 1:5
2.3 ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ መሆን
 ሮሜ 6:1-6

3 መጠመቅ ያለበት ማነው ?

በኢየሱስ ያመነ /የዳነ/ ሐዋ 8:12

4 ሰው መጠመቅ ያለበት መቼ ነው? ሐዋ 8:36-39

4.1 ማመኑን እርግጠኛ ሲሆን
4.2 ለመጠመቅ ፈቃደኛ ሲሆን

5 መጠመቅ ለምን ያስፈልጋል ?

5.1 ትዕዛዝ ስለሆነ::
5.2 ለትእዛዙ ምላሽን በመስጠት ማመናችንን ለሌሎች የምንመሰክርበት ስለሆነ :: ሐዋ 2÷38 -41

**ለአገልጋዩ**

የምንጠመቀው ለመዳን እንዳይደለ አስረዳው ::

6 በማን ስም እንጠመቃለን?

በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም
ማቴ 28:19

7. ማጥመቅ ያለበት ማነው ?

ቤተክርስቲያን ወይንም ቤተክርስቲያን አምና ይህንን ስልጣን የሰጠችው አገልጋይ ፣

**ለአገልጋዩ**

*ሐዋርያት በጌታ ኢየሱስ ስም ስለማጥመቃቸው ከእነዚህ ጥቅሶች በመነሳት ዓላማውን ግለጽ*



*አድርገለት::*
*ሐዋ 2:38 ሐዋ 8:14*

**የምዘና ጥያቄ ሃያ አራት**

1. ጥምቀት የሚለው የቃሉ ትርጉም ምንድነው ?
2. ለመጠበቅ የሚችለው ምን ዓይነት ሰው ነው ?
3. መጠመቅ ለምን ያስፈልጋል?
4. ለመጠመቅ ተዘጋጅተሃል ?
5. በዚህ ትምህርት ውስጥ ያጠናኸውን የቃል ጥናት ጥቅስ ፃፍ::

## ትምህርት ሠላሳ

## የጌታ እራት

**የትምህርቱ ዓላማ**

በዚህ መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ያለውን በረከት ካለመረዳትና ስለ ጌታ እራት ምንነት ካለማወቅ የተነሳ አማኙ በርኩቱን ሳያገኘው እንዳይቀር /እንዳይከለከል/ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ለዚህ የአዲስ ኪዳን ሥርዓት መሠረት ለማስያዝ ነው::

**የቃል ጥናት ጥቅስ** : 1ኛ ቆሮ 11፥27

*"ሳይገባው ይህንን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ስጋና ደም ዕዳ አለበት "*

## 1. የጌታ እራት ምንድነው ?

የጌታ እራት አማኞች በህብረት የጌታን ሞትና ትንሳኤ ለማሰብና ለመናገር የሚቆርሱትና የሚጠጡት በጌታ የተሰጠ የአዲስ ኪዳን ሥርዓት ነው።

## 2. የጌታ እራት አጀማመር

2.1 ይህ ሥርዓት የተጀመረውና ለቤተክርስቲያን የተሰጠው በራሱ በጌታ ነው። ሉቃ 22:14-20

2.2 ጳውሎስም ይህን ከጌታ የተቀበለውን ሥርዓት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዴት መከናወን እንዳለበት አስተማረ።
1ኛ ቆሮ 11:17-33



2.3 የጥንቷ ቤተክርስቲያን እንደ ዋና ዋናዎቹ የቤተክርስቲያን ተግባራት አድርጋ ትተባበር ነበር።
ሐዋ 2:42 , ሐዋ 20:7

## 3. የጌታ እራት በህብረት መቁረስና የሚሰጠው ጥቅም።



3.1 የጌታ እራት የጌታን ሞትና ትንሳኤ እንድናስብ ይጠቅመናል። ሉቃ 22:19
3.2 የጌታን ሞትና ትንሳኤ እንድንናገር ያደርገናል። 1ኛ ቆሮ 11÷26
3.3 በአማኞች መካከል ያለውን ህብረት ለማጽናት። 1ኛ ቆሮ 10:16-17

## 4. የጌታን እራት እንዴት እንካፈላለን?

4.1 በፍቅርና በህብረት በመሰብሰብ። 1ኛ ቆሮ 10:16-17
4.2 የጌታን ሞትና ትንሳኤ በማሰብ። 1ኛ ቆሮ 11፣24-25
4.3 የጌታን እራት አስፈላጊነት በመረዳት።
1ኛ ቆሮ 11:29

## 5. የጌታን እራት መውሰድ ያለበት ማነው?

5.1 የጌታን እራት ለመውሰድ የተገባው ወይም በክርስቶስ ያመነ። 1ኛ ቆሮ 11:27
5.2 የጌታን እራት ምንነት የተረዳ /መለየት የቻለ/ ።1ኛ ቆሮ 11፣29

**ለአገልጋዩ :**

*በዚህ ክፍልጥናት ውስጥ በተለይ ሁለቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችን ዝርዝር ጥናት ብታደርግ ትምህርቱን የበለጠ ግልጽ ያደርግልሃል።*

1ኛ. ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ስድስት ከቁ.25-71
2ኛ. 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አስራ አንድ ከቁ.17-34

**የምዘና ጥያቄ ሃያ አምስት**

1. የጌታ እራት ምንድነው ?
2. የጌታ እራትን መውሰድ የሚችል ምን ዓይነት ሰው ነው?
3. የጌታን እራት ስንወስድ ማድረግ ያለብን ምንድነው?
4. የጌታን እራት ለመውሰድ ተዘጋጅተሃልን? ለምን ?
5. በዚህ ትምህርት ውስጥ ያጠናኸውን የቃል ጥናት ጥቅስ ፃፍ።



መጽሐፏ አንድ ለአንድ በክትትል ወይም በቡድን ሰብስበው ደቀመዝሙር ለማድረግ ለሚፈልጉ ሁሉ በተለይ ለወንጌል አገልጋዮች በየትም ሥፍራ ሆነው ሊጠቀሙባት የምትችል ናት::

መጽሐፉንና ሥልጠና የሚፈልጉ ሁሉ በአድራሻችን ያገኙናል:: አድራሻ- ☎ 61 29 78. 09 21 58 82 ✉ 110152

Africa Printing Press